ድል ነሺ ሕይወት

በዎች ማን ኒ

ተርጓሚ ነብዩ ኢሳይያስ

አሳታሚ፡- ሕይወት ሥነጽሑፍ አገልግሎት
ፖ·ሣ·ቁ· 698 ስልክ 13 15 70
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
ጥቅምት 1990 ዓ/ም

የመጀመሪያ ዕትም ጥቅምት 1990 ዓ/ም
ሁለተኛ ዕትም ሚያዝያ 1990 ዓ/ም

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
All Rights Reserved
First Edition October 1990 (1997)
Second Edition April 1990 (1998)

ይህ መጽሐፍ የተተረጎመው
The Life that win's by Watch Man Nee
copyright 1986
Christian Fellowship publishers, Inc.
New York. U.S.A
ከሚለው መጽሐፍ ነው ።

Published - by Heywet Literature services
P.O.Box 698 Tel 13 15 70
Addis Ababa, Ethiopia
October 1997

ማውጫ

መቅድም

ገጽ

1. ልምምዳችን 7

2. የክርስቲያን ሕይወት በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተገለጸው..... 20

3. የድል ሕይወት ባህርይ.....35

4. ወደ ድል ሕይወት እንዴት እንደሚገባ 53

5. መተው 70

6. እምነት 84

7. የእምነት ፈተና 99

8. ማደግ.....112

9. የድል ድምፀት 129

10. መለየት.....141

መቅድም

ድል ነሺ ሕይወት ምን ዓይነት እንደሆነ ታውቃለህ? ስለምትኖረው የክርስትና ሕይወት ዓይነት በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ታፍራለህ? በክርስትና ሕይወት ኑሮህ ውስጥ ድል ለመንሣት ስትጥር በሚያሳዝን ሁኔታ ወድቀህ እንደ ጳውሎስ «እኔ ምንኛ ጕስቋላ ሰው ነኝ፣ ለዚህ ሞት ከተሰጠ ሰውነት ማን ያድነኛል?» ብለህ ጮኸኻል? ሮሜ 7:24። እግዚአብሔር አብን በጌታችን በኢየሱስ በኩል አመስግን። ድል ነሽ ሕይወት በጥረትና በትግል የሚገኝ ሳይሆን ከራሱ ከእግዚአብሔር የሚሰጥ ነው። ሮሜ 7:25

ድል ነሺ ሕይወት ከጌታ ለአማኞች የተሰጠ ነው። ይህ በጥቂቱ የተለወጠ ሳይሆን ፈጽሞ የተቀየረ ሕይወት ነው። ድል ነሺ ሕይወት ያለፈውን ባህርይ በመጫን የሚመጣ ሳይሆን አዲስ የሚገለጥ ሕይወት ነው። ድል ነሺ ሕይወቅ በውስጥህ በሚኖረው በክርስቶስ እንጂ በራስህ ጥረት የሚገኝ አይደለም። በእግዚአብሔር ልጅ በኢየሱስ ክርስቶስ ስታምን እግዚአብሔር የሰጠህ አንተም የተቀበልከው እንዲህ ያለ ሕይወት ነው። ከእግዚአብሔር ጋር የቀረበ ኅብረትን የሚፈጥር ኃጢአትን ድል የነሣ ሕይወት ነው። ይህ ሕይወት እርካታና ሰላም እንዲሁም ኃይል የሞላበት ሕይወት ነው። ይህ በአንተ ውስጥ ሆኖ መገለጥን የሚጠብቀው ሕይወት እንዴት ይመጣል ብትል በምትከህ ክርስቶስ እንዲኖር በመፍቀድ ነው። ይህ እምነት የሚጠይቅ ጎዳና ነው እምነቱም ለመዳን ያመንከውን ዓይነት ነው። ከዚህ በኋላ በወደደህ በእርሱ ከአሸናፊዎች ትበልጣለህ። ሮሜ 8:37

ይህን ድል የሚነሣ ሕይወት አማኞች እንዲለማመዱት ይረዳቸው ዘንድ ዎችማን ኒ «ድል ነሽ ሕይወት» በሚል ርዕስ ላይ በርካታ ተከታታይ መልእክቶችን እ.ኤ.አ. 1935 ዓ.ም. በመስከረምና በጥቅ ምት ወሮች በቻይና ውስጥ ሻንጋይ በምትባል ከተማ በተደረገው ኮንፍራንስ ላይ ተናግረዋል። ዎችማኒ እንደ ወትሮው ሰፊና መንፈሳዊ

ጥልቀት ባለው ትምህርታቸው በቀላልና ግልጽ በሆነ መንገድ በዚህ ቋሚ ርዕስ ላይ ሙሉ በሙሉ አስተምረዋል።

ዎችሚ በዚያ ከንፍራንስ በሚያሳፍር ሁኔታ ከሚገባው በላይ በዘቀጠው በአማኙ የግል ልምምድ ላይ ነው ትምህርታቸውን የጀመሩት። ከዚያ በኋላ በንፅፅር ከእግዚአብሔር ለአማኙ የተሰጠውን የክርስትና ሕይወት አስረዱ፣ ቀጥሎም ወደዚህ ሕይወት የምንገባበትን መንገድ ከግሣየታቸው በፊት የዚህን ሕይወት ምንነት በበለጠ አስተማሩ፣ ዘረዘሩም። የድል በር ግጥረሚ መንገዶች ለምን እንደሚሰውሩብን ምክንያቶችን አብራሩ። በመቅጠልም ስለ እምነት መፈተን ለእድግሎታቸው አስጠነቀቁ። አማኞች በእግዚአብሔር ጸጋ እንዲያድጉ መከሩ፣ የድል ድምጽ የሆነው ምስጋና እንዲኖርም አጽንተው ገለጡ። በመጨረሻም ከድል በኋላ የመጀመሪያና የመጨረሻ ድርጊት በሆነው የመቀደስ ወይም የመለየት ውጤት ደመደሙ። አሁን እነዚህ መልእክቶች ለመጀመሪያ ጊዜ ከእንግሊዘኛ ወደ አማርኛ ተተርጉመው ለአንባቢያን ቀርበዋል።

የክብር አምላክ የራሱን ሕይወት በኛ ውስጥ በማናሩ ይክበር።

«ሁሉ ከእርሱና በእርሱም ነውና ለእርሱ ለዘላለም ክብር ይሁን አሜን» ሮሜ. 11–36

ተርጓሚው

ስለ መጽሐፉ

በሐገራችን የክርስቲያን ሥነጽሑፍ ረድፍ የትርጉም ሥራዎች ያዋሉት አስተዋጽኦ የሚያስመሰግን ሲሆን፣ ከታላት ገበያው ጀምሮ የሃጉብ ተዋረድን በመጠበቅ በሁለት ሕብረተሰብ መሐከል ያለውን የባህልና የአገላለጽ ልዩነቶችን በግጥበብ፣ የመጽሐፉን ለዛ ሣያዛንፉ ለውጤት መብቃት በራሱ የሚያስተምነው ዋጋ ሚዛኑ ይደፋል። የዚህ መጽሐፍ ተርጓሚም ለሃገራችን አንባቢ በሚስማማ መልክ ይህን መጽሐፍ ለማቀነባበር ያደረገው ጥረት እድካሚ ነበር።

መጽሐፍ ቅዱስ የክርስትናን ሕይወት በራሣችን ጥረት እንደማንኖረው፣ በራስ ትግልም ቅድስና እንደማይቃና አጥርቶ ቢያስተምርም እውነታውን ደጋግመን የምን ስተው ጥቂቶች አይደለንም። የጨለማው አለቃ ሰይጣን ሰዎችን የሚሸነግልበት፣ የሚከስበትና የቅጥፈት ብልጣብልነቱን የሚያሣይበትና በዓለማችን ያሉ የበርካታ ሃይማኖቶች አንደኛው መታለልም ቅድስናን በእኛነታችን ትግል ለማግኘት የሚደረገው ግብግብ ነው።

ሰዎች ከእውነታው ተራርቀው ጥረት ባጀበው ምግባረ ሰናይነት እግዚአብሔርን ለማክበርና ለማስደስት ከሞከሩ ውጤቱ ተስፋን ማጨጠጥ ይሆናል። ይህ መጽሐፍም እግዚአብሔር ያዘጋጀልን ድል ነሺ ሕይወት በትንቅንቅና መፍጨርጨር የሚገኝ ሣይሆን እንደ ደህንነታችን ሁሉ በእምነት የምንቀበለው መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስን ባማከለ መልኩ ያብራራል።

መለኮታዊው የእግዚአብሔር ፈቃድ ከመጀመሪያውም ሆነ ዛሬም ሰዎች በእግዚአ ብሔር ላይ ብቻ በመታመን እንድንኖረው ተደርጉ የተቀናጀ ነው። በዓለም ዙሪያ በመጽሐፍቶቻቸውና በትምህርቶቻቸው ታዋቂና ተወዳጅ የሆኑት አገልጋይና የበርካታ መጽሐፍት ፀሐፊም የሆኑት ዎች ማንኒም ሊያሣዩን የሚወዱት ይህንኑ የቀላል ሕይወት እውነታ ነው።

ነብዩ ኢሣይያስ ለትርጉም የመረጠው ይህ መጽሐፍ የክርስትና ሕይወት አብይ ጭብጥ የያዘና በብዙ ኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች ሕይወት ውስጥ ስኬታማ ሥር ነቀል ለውጥን የሚያመጣ እንደሚሆን ጥርጥር የለኝም።

ተርጓሚው በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ሰፋ ያለ ጥናት እንዳደረገ በተደጋጋሚ ያስተምራቸው ከነበሩት የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችና ይህን መጽሐፍም በአርታዒነት ስሠራለትም ለመረዳት ችያለሁ። በትርጉም ሥራው ውስጥ ያሣየው ጥረት የሚያበረታ ታና ሌሎችንም የሥራ ውጤቶችን እንዲያቀርብልን ይላመድህ የሚያሰኘው ሆኖ አግኝቼዋለሁ።

ደረጀ አበበ

ምዕራፍ አንድ

ልምምዳችን

«እንግዲያስ መልካሙን አደርግ ዘንድስወድ በእኔ ክፉ እንዲያድር ብኝ ሕግን አገኛለሁ።» ሮሜ 7:21 «ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና፤ የእግዚአብሔርም ክብር ጕደ ኵአቸ ዋል፤ በኢየሱስ ክርስቶስም በሆነው ቤዛነት በኩል፤ እንዲያው በጸጋው ይጸድቃሉ።» ሮሜ. 3:23

ለክርስቲያኖች የተሰጠ ሕይወት

ቅዱሳት መጻህፍት እንደሚነግሩን ለክርስቲያኖች ከእግዚአብሔር የተሰጠው ሕይወት ፍፁም ደስታና ዕረፍት ያለበት፤ ከእግዚአብሔርም ፈቃድ ጋር ፍፁም የተዋሐደ ሆኖ እናገኘዋለን። ይህ ሕይወት ዓለምን የማይራብና የማይጠማ ከኃጢአት ውጭ የሚራመድና ሁሉን ነገር ሰን ጥቆ የሚያልፍ ሕይወት ነው። ይህ ሕይወት ቅዱስ፤ ኃይለኛ፤ ድል ነሽና የእግዚአብሔርን ፈቃድ በማወቅ ከእርሱ ጋር የማያቋርጥ ግንኙት የሚያደርግ ሕይወት ነው።

እግዚአብሔር ለክርስቲያኖች የሰጠው ሕይወት ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር በእግዚአብሔር ውስጥ የተሰወረ ነው። ይህን ሕይወት ምንም ነገር አይነካውም፤ አይጐዳውም፤ አያናውጠውም። ክርስቶስ ሁሉን አልፎ እንደሚሄድ እኛም ሁሉን አልፈን እንሄዳለን። ክርስቶስ በእግዚአብሔር ፊት እንደሆነ እኛም በእርሱ ፊት ነን። ስለዚህ እንደክግለን፤ እንሸነፋለን የሚል ነገር ሁለተኛ በሃሣባችን አናስተናግድ፤ መድከም ወይም መሸነፍ የሚባል ነገር የለም። ምክንያቱም በቆላ. 3:4 ላይ እንደተፃፈው «ክርስቶስ ኢየሱስ ሕይወታችን ነውና»። ክርስቶስ ኢየሱስ ሁሉን ያል ፋል፤ በምንም ነገር ሊሸነፍ፤ ሊያዝ አይችልም። የክርስቶስ ሕይወት ይህ ነው። ሃሌሉያ!

የተሰጠን ሕይወት ዕረፍት፣ ደስታና ኃይል የሞላበትና የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈፀም የሚችል ነው። እስቲ ዛሬ ምን ዓይነት ሕይወት እንደምንኖር እንጠይቅ። ሕይወታችን እግዚአብሔር እንድንኖረው የሰጠን ዓይነት ካልሆነ ድል ምን እንደሆነ እንደሚገባ ማወቅ ይኖር ብናል። ስለዚህ ልምዳችንን በተመለከተ አንዳንድ እውነቶችን ከዚህ በታች አብረን እንድንመለከት እፈልጋለሁ። እነዚህ እውነታዎች ለአንዳንዶቻችን ላይስማሙ ይችላሉ፣ ነገር ግን በእግዚአብሔር ቃል እውነትነታቸው ልንቀበላቸው ይገባል። ጉድለታችንን ተረድተን ጸጋን ከእግዚአብሔር መለመንና መቀበል እንድንችል እግዚአብሔር ይርዳን።

በክርስቲያኖች ሕይወት ውስጥ ያሉ ስምንት ዓይነት ውድቀቶች

ምን ዓይነት ሕይወት ነው የምትኖረው? በኃጢአት ባርነት ሥር? ሐዋርያው ጳውሎስ በሮሜ 7:18 ላይ እንዲህ ይላል «በእኔ ማለት በሥጋዬ በጎ ነገር እንዳይኖር አውቃለሁና፣ ፈቃድ አለኝና መልካሙን ግን ማድረግ የለኝም» ይህ በእኛ በአማኞች ልምምድ ውስጥ እውነት ነው። እግዚአብሔር በክርስቶስ የከበረ ድል አድራጊ ሕይወት ሰጥቶን ሣለ እኛ ግን በሽንፈት ሕይወት እንኖራለን። በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ እንደ ተፃፈውና በልምምዳችንና በምርምሮችም እንደተረጋገጠው በክርስቲያኖች ሕይወት ውስጥ ስምንት ዓይነት ውድቀቶች ወይም ኃጢአቶች ይገኛሉ ብለን መደምደም እንችላለን።

1. የመንፈስ ኃጢአቶች

ትዕቢት፣ ቅንዓት፣ አለማመን፣ ስህተት ፍለጋ፣ የጸሎት ማነስና ራስን ለእግዚአብሔር አደራ አሣልፎ አለመስጠት፣ እነዚህ ሁሉ የመንፈስ ኃጢአቶች ናቸው። ምንም እንኳ አንዳንድ አማኞች በመንፈሣዊ ሕይወታቸው ድል አድራጊዎች ቢሆኑም ሌሎች ደግሞ በእነዚህ ኃጢአቶች የተሸነፉ ናቸው።

በአንድ ወቅት የትዕቢት ኃጢአት አስቸግሮኝ ነበር። ኩሩዎች ሁሉ የዚህን የመንፈስ ኃጢአት ፈጽመዋል። ኩሩ ሰው ሌሎች ከእርሱ ሊበ

ልጡ እንደሚችሉ ማየት አይችልም። ይህ በዓለማውያን ብቻ ሣይሆን በክርስቲያኖችም ላይ የሚታይ ነው። ሌላ ሰው የሚበልጠው ሲመስለው ሁልጊዜ ስህተት ይፈልጋል። ዝቅ ሊያደርገውም ይሞክራል።

ቅንዓት በሥራም ሆነ በመንፈሣዊ ነገሮች ቢከሰት ኃጢአት ነው። አንዳንዶች ደግሞ ባለማመን ክፉ ልብ ተሞልቶዋል። አንድ አማኝ በእግዚአብሔር የሚያምን መሆኑን ቢጠየቅ የሚያምን መሆኑን ይመልሳል፤ ነገር ግን በአጸደፈታው በተስፋ ቃሉች ላይ በእውነት የሚያምን መሆን አለመሆኑን ቢጠየቅ የማያምን ሆኖ ያገኛል። በጣም ትንሿ ፈተና ታና ውጠዋለች። ምክንያቱም የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃሉች ሊያምን አልቻልምና ነው። በአንድ ወቅት ማርቲን ሉተር በጣም አዝኖ ስለነበረ ሚስቱ የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃሉች ለማመን ተሸንፎ ስላየችው የሐዘን ልብስ ለበሰችና፤ «ዛሬ የሐዘን ልብስ ለብሻለሁ ምክንያቱም ልክ እምላ ከሀ እንደ ሞተ ያህል በጣም ተጨንቀሃልና» ስትል ተናገረችው በእኛም ዘመን ይኸው እውነት ነው።

ብዙዎች በእግዚአብሔር ተማምነው አይኖሩም። ከእርሱም ጋር መልካም ግንኙት የላቸውም፤ በግድ የለሽነትም ይኖራሉ። ብዙ ቀናትም ያለ ጸሎትና ያለ መጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ያሳልፋሉ። ከእግዚአብሔር ጋር ማምንቱን ሙሉ ሣይገናኙ ቀን በቀንም ጌታን ሣይፈሩ ይመላለሳሉ። ይህም በእግዚአብሔር ፊት የማይኖሩ መሆናቸውን ያሣያል። እንዲህ ዓይነት አማኞች የተትረፈረፈ ሕይወት የላቸውም። ራሰንም መግዛት በሚጠይቅ ነገር ላይ የተገዛ ማንነት የላቸውም፤ ፈጽሞም ራሣቸውን አልካዱም።

ችፎ በምትባል ቦታ ውስጥ አብረው የሚኖሩ ሁለት ወንድሞች በማይረባ ነገር ተጣልተው እንደነበረ ትዝ ይለኛል። አብረው በበሉ ቁጥር አንደኛው ወንድም ከምግቡ ውስጥ ደህና ደህናውን ሥጋ እያነሣ ይጨላ ነበር። ሌላው ወንድም ይህንን ድርጊቱን ተመለከተና አንድ ሁለት ማምንት ዝም አለው። ከሁለት ማምንት በኋላ ግን ከዚህ በላይ ነገሩን መታገስ አልቻለምና ራሱን ከዚህ ወንድም ለየ። እዚህ ላይ በትልልቅ ነገሮች ሣይሆን በትንንሽ ነገሮች የሰዎች ማንነት ሊገለጥ እንደሚችል መመልከት እንችላለን። በዚህ ረገድ ያነበብኩትን የሀድሰን ታይለርን

የሕይወት ታሪክ አስታውሳለሁ። ይህ ወንድም ወንጌል ለመስበክ በሚዘዋወርበት ቦታ ሁሉ የማይረባ ክፍልና አልጋ ይደርሰዋል፤ ይህም ቢሆን ግን ይህ የእግዚአብሔር አገልጋይ ለአንድም ቀን እንኳ በፍፁም ተግሮና አጉረምርሞ አያውቅም። ይህ ቀላል ነገር ቢሆንም የአንድ ሰው ስሜት በትንሽ ነገር ሊጐዳ ይችላል። ሕይወቱ በእግዚአብሔር ፊት ምን ዓይነት እንደሆነ ያሳየናል።

2. የሥጋ ኃጢአቶች

የመንፈስ ብቻ ሣይሆን የሥጋም ኃጢአቶች አሉ። እነርሱም ዝሙት፣ ቅብዝብዝነት እንዲሁም ተገቢ ያልሆነ ወዳጅነትና ግንኙነቶች የመሳሰሉት ናቸው ብዙዎች በእነዚህ ኃጢአቶች ይወድቃሉ። አንዳን ዶች ዝሙትን በመፈፀም በገዛ ሰውነታቸው ላይ ኃጢአትን ይሠራሉ። እንዲሁም ሌሎች በዓይናቸው ኃጢአትን ይሠራሉ። ብዙዎች ደግሞ ከማያምኑ ጋር ተገቢ ያልሆነ ጓደኝነት ይመሠርታሉ።

ዓይኖችህን ተቆጣጥርህ ታውቃለህ? በዚህ ዘመን በዓይን ብዙ ነገር የማየት ሉጋጣሚ እንዳለ አውቃለሁ። ዓይኖቻቸውን መቆጣጠር ባለመ ቻላቸው ወደ ድል መምጣት ያልቻሉ ብዙ ክርስቲያኖች አሉ። ይህን በተመለከተ ግን በእግዚአብሔር ፊት አንድ ነገር ማድረግ አለብን። ወዳጅነትም እንዲሁ ሊታሰብበበት የሚገባ ነገር ነው። በአንድ ወቅት አንድ ወንድም ከማያምን ሰው ጋር አጥብቆ ወዳጅነት ያዘ። ይህ ሁኔታ በዓለም አመለካከት እንደ ኃጢአት አይታይም። ክርስትያኖች ለሆንን ግን ኃጢአት ነው። አንድ ሚሲዮናዊን አንዱ ቀርቦት ከሁሉ በላይ ጓደኛዬ ላድርግህ እንዳለው መስክሮልናል። ከተገቢው በላይ ከማያምኑ ጋር ወዳጅነት መመሥረት የተከለከለ ነው። 2ኛ ቆሮ. 6:14

3. የአእምሮ ኃጢአት

ብዙዎች የመንፈስ ኃጢአት ላይፈጽሙ ይችላሉ። ሥጋቸውም ተገ ዝቶ ሊሆን ይችላል። በአእምሯቸው ግን ድል የላቸውም። ሃሣባቸው ከኃ ጢአት ነፃ አይደለም፤ ወጣ ይላል፤ ይነሆልላል፤ ይበተናል። ንፁሕ አይ ሆንላቸውም፤ ይቆሸሽባቸዋል፤ ወይም ደግሞ በጣም ግምታዊና በጥር

ጣሪ የተሞላ አለትጥ ለማወቅም የሚጓጓ ይሆንባቸዋል፤ ባወቁት አይረ ኩም። የማይታወቀውን ለምን አይታወቅም ይላሉ። እንዲህ ዓይነት አእ ምሮ ያላቸው ሰዎች ወደ ድል ነሽ ሕይወት አይገቡም።

እንደ እውነቱ ከሆነ በአእምሯቸው ድልን የሚለማመዱ አማኞች በጣም ጥቂቶች ናቸው። በአንድ ወቅት ሃጣቢ ለምን እንደሚነሆልልባት ያልገባት አንዲት እህትና ሃጣቡ ሁልጊዜ እንደሚቆሽሽበት የመለከረ አንድ ወንድምም አጋጥመውኛል። መንፈሳዊውን ሕይወት ለመኖር በዚህ አካባቢ መፍትሔ ማግኘት አለብን።

ግምትና ጥርጣሬ ብዙ ክርስቲያናችን ጐድቷል። ለምሳሌ ፊቱ የጨ ፈገገ አንድ ወንድም በመንገድ ላይ ብታገኝ ወዲያውኑ የምትገምተው ምንድነው? በእኔ ላይ ደስተኛ አይደለም ነው የምትለው፤ ነገር ግን ቤቱ አብረኸው ብትሄድ ባለፈው ሌሊት ደህና እንቅልፍ እንዳልተኛና ራሱን እንዳመመው ይነግርሃል። ነገር ግን በአንተ ላይ አንድ ደስ ያላለው ነገር እንዳለ ገምተሃል! እውነቱ ግን ያ አይደለም።

በግምት ምን ያህል ተጐድተናል? ያም ሆኖ ግን ራሳችንን እንደ መርግሪ አድርገን እንቆጥራለን። ኩላሊትንና ልብን የሚመረምር ጌታችን ብቻ መሆኑን እናስታውስ። ራዕይ 2:23 ብዙዎች በስህተት እገሌና እገሊት እንዲሆና እንዲያ ናቸው ይላሉ። እንዲህ በማድረግ በአእምሯ ችንም ኃጢአት ሠርተናል። ለራሳችን ጥቅም ለማምጣት በሰዎች ላይ ብዙ ፈርደናል! ብዙም ገምተናል። ስለ አእምሯችን በእግዚአብሔር ፊት መፍትሔ ማግኘት አለብን፤ ያለበለዚያ በምን ተአምር ነው ወደ ድል ነሺ ሕይወት የምንመጣው?

አንድ ወንድም ልክ በሌለውና ባልተገራ የማወቅ ፍላጐት ተሞልቶ ነበር። የሁሉንም ነገር ምክንያት ማወቅ ስለነበረበት ሁሉን ተነተነ፤ መረ መረ አእምሮው ግሰብ ከሚገባው በላይ ስላወቀ በመጨረሻ በጥርጣሬ ተሞላ።

4. የሰውነት ወይም የአካል ኃጢአት

በአካል ላይ የሚፈጽሙ አንዳንድ ድርጊቶች በዓለም ችላ ሊባሉ ይችላሉ። ለመንፈሣዊ ነገር ራሱን ላስገዛ ክርስቲያን ሕይወት ግን ኃጢ

አቶች ናቸው። አንዳንድ አማኞች ለመብል፣ ለመጠጥ ወይም ለመሸቀርቀርና ለእኔነታቸው ከፍተኛ ትኩረት ይሰጣሉ። በእግዚአብሔር ዓይን እነዚህ ኃጢአቶች ሊሆኑ ይችላሉ።

ብዙ ክርስቲያናች የግድ መብላት አለባቸው። ክርስቲያን ከሆኑ አንስቶ ያመው አያውቁም። ከእነርሱም ጋር በመብላት ምን ዓይነት ሰዎች እንደሆኑ አበላላቸው ወዲያውኑ ይነግርሃል። ቢላዋና ሹካ ሲያነሱ እነማን እንደሆኑ ታውቃቸዋለህ። ለምሳሌ አንድ ጊዜ ያገኘሁት ወንድም የምግብ ፍላጐቱ ከመደበኛው የሰው የምግብ ፍላጐት ምን ያህል ትልቅና ልዩ እንደሆነ ነግሮኛል። በአመጋገብ ላይ ራስን ያለመግዛት ኃጢአት ሊሆን እንደሚችል ሣልናገር አላልፍም።

አንዳንዶች ከተለመደው የመኝታ ሰዓት ጥቂት አሣንሰው ከተነሱ ወዲያውኑ ሐዘንተኞች ይሆናሉ። ከዚህ የተነሣ በሥራ ላይ ይጣደፋሉ፣ ንግግራቸው የተምታታ ይሆናል፤ ይህም ኃጢአት ነው። አንዳንዶች ማጌጥ በጣም ይወዳሉ። ይህ ሁሉ ምንድነው? እኔነትና የራስን ሕይወት መውደድ አይደለምን? ጥቂት መከራ መታገስ ወይም ወደ በሽተኛ በጣም ፡ ፡ቅረብ እስክ ማይችሉ ሕይወታቸውን የሚወዱ ብዙዎች አሉ። በግልጽ ለማስቀመጥ ለሰውነታቸው ባርያዎች ናቸው። ጳውሎስ ግን እን ዲህ ብሏል፣ «ሥጋዬን እየጐሰምሁ አስገዛዋለሁ» 1ኛ ቆሮ 9፥27። ሰውነታችን እንዲገዛን ከፈቀድንለት ያ ኃጢአት ነው። ሰውነታችን ከእኛ በታች እንጂ በላይ መሆን የለበትም። ብዙዎች መተኛት ስለሚፈልጉ የማለዳ ጸሎትን ችላ ይላሉ። ሌሎች ደግሞ መብላትና መሽቀርቀር ስለሚወዱ እግዚአብሔርን ማገልገል አልቻሉም። ስእነዚህም የሰውነት ፍላጐቶች ምክንያት ራስን አለመግዛት ኃጢአት ነው።

5. የባህርይ ኃጢአት

ባህርይ ማንነትን የሚያመለክት ነው። ሁሉም ሰው የተወለደው በተለ ያየ ዓይነት ባህርይ ነው። በተለያየ ዓይነት ባህርይ መወለዳችን በማንነ ታችን ውስጥ ልዩ ባህርይን ይፈጥራል። ሆኖም ግን ጌታ ከባህርያችንና ከኃጢአታችን ሊያድነን መጥቷል። አንዳንድ ሰዎች በግትረኝነትና በቀላሉ በሚገነፍል ባህርይ የተወለዱ ናቸው። ሌሎች ደግሞ በጽድቅ

አመለካከት ተወልደዋል። ይህ የኋለኛው ዓይነት ባህሪይ ያለው ሰው በሁሉም ዓይነት ጉዳዮች ለሁሉም ሰዎች በማንኛውም ጊዜ እንደ ጠቅ ላይ ፍርድ ቤት ዳኛ ይሆናል። በጣም ፃድቅና ቅን ሊሆን ይችላል። ነገር ግን በወንድሞች መካከል በሚያደርገው ነገር ጣፋጭነት ይጐድለዋል። ሁልጊዜ ትክክለኛ ነው። ነገር ግን ኃይለኛ ነው። ይህም ደግሞ ኃጢአት ነው እላለሁ።

ኮሰታራ ከሆነው ፃድቅ ሰው ተቃራኒው ደግሞ በጣም ደካማ የሆነ ሰውና በሁሉ ነገር የሚፈራ ሰው ነው። እንዲህ ላለ ሰው ሁሉ ነገር ትክክል ነው። እንዲህ ዓይነቱ ፃድቅ መሣይ ሰው ሰዎች ሁሉ እንደ ፃድቅና ቅዱስ ሊቆጥሩት ይችላሉ። ነገር ግን ከዚህ የሚከተለውን ጥያቄ እያን ዳንዳችን መጠየቅ አለብን። ባህሪያቸው ፃድቅና ቅዱስ ከሚመስሉት ሰዎች ውስጥ ምን ያህሉን ሰዎች እግዚአብሔር ተጠቅሞባቸዋል? የእግ ዚአብሔር ልጅ በምድር ላይ በነበረ ጊዜ እንደነዚህ ፃድቅ ይመስል ነበረን? መልሱ በግልጽ አይደለም ነው። በእነዚህ ሁለት ዓይነት ሰዎች ሕይወት ውስጥ የተገለፀው የባህርይ ኃጢአት መወገድ አለበት።

ሌላም ደግሞ አለ። ግትር ወይም ለስላሳ ያልሆነ ባህርይ ያለው ሆኖም ግን በሁሉም ነገር ራስ መሆን የሚፈልግ ነው። እንዲህ ዓይነት ባህርይ ያለው ሰው በተገኘበት ቦታ ሁሉ ራሱን ማሣየት ይፈልጋል። ምንም ዓይነት ሁኔታ ይሁን ሁልጊዜ መናገር ወይም የትኩረት ማዕከል መሆን እንዳለበት ያምናል። በሰዎች እስኪታይ አይረካም። እንዲህ ዓይነቱ የተደበቀ የእግዚአብሔር ሰው መሆን አይችልም። አሁንም ሌላው አማኝ በጣም ዓይናፋርና ሰዎችን ሁሉ የሚሸሽ ነው። በሄደበት ቦታ ሁሉ እርሱ ወይም እርሷ ጥግ ቦታ ላይ ይቀመጣሉ። ወደ ፊት ወንበ ሮች መምጣትና መቀመጥ አይሆንላቸውም። ይህ ደግሞ መጥፎ ባህርይ በመሆኑ መስተካከል አለበት።

አንዳንድ ክርስቲያኖች ቶሎ ተናዳጆች ናቸው በአንድ ወቅት አንድ ወንድም እንዲህ አለ፤ «እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ ቶሎ እናደዳለሁ ቶሎም ከቁጣዬ እበርዳለሁ። ጠዋት ላይ እናደድ ይሆናል፤ ከአምስት ደቂቃ በኋላ ግን ሁሉ አልፎአል፤ ቢሮም ስደርስ ሁሉንም እረሣለሁ»። በዚህ ወንድም ቁጣና ንዴት ሚስቱና ልጆቹ ቀኑን በሙሉ ሲረብሹ ነው

የሚውሉት። ነገር ግን ወደ ቤቱ ሲመለስ ሚስቴ ለምን አዘነች? ብሎ ይገርመዋል። እርሱ ደህና ሆኖ ሣለበቤተሰቡ ግዘን በጣም ይደነቃል። ይህ የባህርይ ኃጢአት ነው። በመሆኑም መወገድ አለበት።

አንዳንዶች በቀላሉ ሊሠራ የሚችልን ሥራ ለቀን ወይም ለአሥር ቀን ሊያቆዩት ይችላሉ። ይህ ስንፍና ነውና መወገድ አለበት። እያንዳንዱ ሰው የየራሱ ባህርይና ተፈጥሮ አለው። በቅዱሳን መካከል የተለያየ ባህርይ ያላቸው ሰዎች አሉ። አንዱ በጣም የሚቆጣ ሲሆን ሌላው ደግሞ በሁሉ ነገር ጠንካራና ጥንቁቅ ነው። ሌሎችን ባያታልልም እርሱን ግን ግንም እንዲያታልለው አይፈቅድም። የሰውን ዓይን ወይም ጥርስ አይ መታም ሌሎች የእርሱን ዓይን ወይንም ጥርስ ሊመቱ ቢሞክሩ ግን ዓይን ስለ ዓይን ጥርስ ስለ ጥርስ ነው የሚያስከፍለው። ቀኝ ጉንጭህን በጥፊ ለሚመታህ ሁሉ ሁለተኛውን ደግሞ አዙርለት የሚለው ምን ማለት እንደሆነ አይገባውም። አንዳንዶች እንደዚህ ሰው አይደሉም። ነገር ግን መካከለኛ ይሆናሉ። ሰዎችን ፊት ለፊት አይዘር ፉም፤ ከሌሎች ግን አምስት ሣንቲም ጥቅም የሚያገኙበት አጋጣሚ ከተ ገኘ ወደ ኋላ አይመለሱም።

አንዳንድ ሰዎች በተፈጥሯቸው ለፍላፊ ሊሆኑ ይችላሉ። እነዚህ ሰዎች ባሉበት ፅጥታ ሊኖር አይችልም። በጣም የሚያሳዝነው ሌሎችን ፀጥታ እስኪነሣ የሚያወሩት ስለ ሌላ ሰው ነው ውሸት የመናገር ሃጣብ ባይኖራቸውም ሁልጊዜ ግን ያጋንናሉ። ባህርያቸው ይህ ነው። እንግዲህ ሁላችንም ይህን እንረዳ። ድል ነሺዎች ለመሆን ከፈለግን በግል ባህርያ ችን ጉዳይ ላይ ጌታ እንዲሠራ እንፍቀድለት።

ለምን ስለነዚህ ነገሮች እንነጋገራለን? ብዙ ክርስቲያኖች የሚኖሩት ኑሮ የእግዚአብሔርን ሕይወት ስለማይመስል ነው። አንዳንድ ወንድሞች የሌሎችን ሰዎች ጉድለት ያያሉ መልካም ነገራቸውን ግን ማየት አይች ሉም። ሁልጊዜ ስለ ወንድሞቻቸው ጉድለት ይናገራሉ። አንድ ጊዜ በዚህ ነገር ላይ ድል ያገኘ ወንድም ድልን ከማግኘቱ በፊት ለምን ሁል ጊዜ በሌሎች ወንድሞች ላይ ስህተትን እንደሚፈልግ ምክንያቱን እንደ ማያውቅ መስክሯል። ወደ ወንድሙ ተመልክቶ ስድስት ወይም ሰባት ጉድለቶችን ያገኛል፤ ወደ ሌላኛውም ወንድሙ ተመልክቶ እንዲሁ።

በመጨረሻ ግን ይህን የሚያደርግበት ምክንያት እርሱ ራሱ እነዚህ ጉድለቶች ስላሉበት እንደሆነ ነገርኩት። የባህርይና የተፈጥሮ ጉድለቶች ስላሉበት እንደሆነ ነገርኩት። የባህርይና የተፈጥሮ ጉድለቶች ኃጢአቶች ናቸው፣ በመሆኑም ክርስቲያን ሁሉ ከእነዚህ ነገሮች በላይ በድል መኖር አለበት። በእነርሱ መሸነፍ የለበትም።

6. የእግዚአብሔርን ቃል የመጠበቅ ልብ ማጣት

ከመጽሐፍ ቅዱስ አንፃር በእግዚአብሔር ፊት የጐደለን ነገር ቃሉን የመጠበቅ ልብ ነው። ይህ ደግሞ ኃጢአት ነው። እስቲ ራሳችንን እንጠይቅ፤ ምን ያህሉን የእግዚአብሔርን ቃል እንዳነበብንና ትዕዛዙን እንደጠበቅን እንዳከበርን። ለምሳሌ ስንቶቹ ባሎችሚስቶቻቸውን ይወዳሉ? ስንቶቹ ሚስቶችስ ለባሎቻቸው ይገዛሉ? አንድ ጊዜ አንዲት እህት ለባሏ መገዛት እንዳለባት እንደምታውቅ ነገር ግን እንደ እግዚአብሔር ቃል በትክክል ተገዝታ እንደማታውቅ ተናግራለች።

ክርስቲያኖች ጭንቀት ምን ያህል ኃጢአት መሆኑን ያውቃሉ? በፊሊ.4:4 ላይ የእግዚአአብሔር ቃል «ሁልጊዜ በጌታ ደስ ይበላችሁ» ብሎ ያውጃል። ስንቶች ክርስቲያኖች ይህንን ትዕዛዝ አክብረዋል? ጭንቀትና መረበሽ ኃጢአት መሆኑን ማወቅ አለብን። መደሰትን የማይቀበሉ አማኞች ሁሉ ኃጢአትን ፈጽመዋል። ምክንያቱም የእግዚአብሔር ትዕዛዝ ለእኛ በአንዳች ነገር እንዳንጨነቅ ነው። /ፊሊ. 4:6/ በሰው ዓይን ፊት ጭንቀት እንደ ኃጢአት ባይቆጠር በእግዚአብሔር ቃል መሠረት ግን ኃጢአት ነው። በሁሉ ነገር ማመስገን አለብን ይህ የእግ ዚአብሔር ትዕዛዝ ነውና በሁሉ ነገር «እግዚአብሔር ሆይ አመሰግንሃለሁ፣ አባርካለሁ»፣ ብለን መፀለይ አለብን። ችግር ቢገጥመን እንኳ እንዲህ ማለት አለብን። ዘጠኝ ልጆች ስላሏት አንዲት እናት የተነገረ ታሪክ አለ «በአንዳች አትጨነቁ» የሚለው ቃል እንደ እርሷ ባለው እናት ላይ ተፈፃሚነት ሊኖረው እንደማይገባ ትከራከራለች፣ ምክንያቱም አለ መጨነቅ ለእርሷ ኃጢአት ሆኗልና። በመጀመሪያ እስኪሞቱ ድረስ ባለማ ቋረጥ የተጨነቀችላቸው ሁለት ልጆች ነበሯት። ቀጥሎም አድገው ለአቅመ አዳም እስኪደርሱ ሰባት ልጆች ነበሯት፣ ያሳዝናል ይህች ሴት

መጨነቅ በእርግጥ ኃጢአት መሆኑን አላወቀችም። ጭንቀት ክርስቲያናዊ ግዴታ መስሏታል።

ሁልጊዜ ደስ እንድንሰኝ የእግዚአብሔር ትዕዛዝ ነው። 1ኛ ተሰ.5: 16 «በሁሉም ነገር እንድናመሰግን» የእርሱ ፈቃዱ ነው። ድል የነሱ ሁሉ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ መጠበቅ አለባቸው። ድል ያልነሱ ግን ፈቃዱን ሊጠብቁ አይችሉም።

7. ለእግዚአብሔር የሚገባውን አለመስጠት

እግዚአብሔር ራሳችንን ከቤተሰቦቻችን ጋር እንዲሁም ከሥራችንና ከሐብታችን ጋር አጠቃለን ለእርሱ እንድንሰጠው ይፈልጋል። ነገር ግን እያንዳንዱ ክርስቲያን የተወሰነ ነገር ለራሱ የሚያስቀር ይመስላል። ምንም እንኳ ብዙዎቹ ኪዳን ሰዎች አንድ አሥረኛውን ለእግዚአብሔር መስጠት ያለባቸው ቢሆንም የአዲስ ኪዳን አሰጣጥ ግን አሥር አሥረኛ ነው። እርሻችንን፣ ሚስቶቻችንን፣ ልጆቻችንንና እኛ ራሳችንንም ጭምር ለጌታ መስጠት አለብን። ሉቃ. 14÷25–26

ብዙ ክርስቲያኖች እግዚአብሔር የሚያስቸግራቸው እየመሰላቸው ይፈራሉ። በአንድ ወቅት ራሱን ለጌታ መስጠት የሚፈራ አንድ አማኝ እንዲህ አለ «ራሴን ለጌታ ብሰጥና እርሱስ እንድሰቃይ ቢያደርገኝ ምን ማድረግ እችላለሁ?» ይህንን ወንድም ኮስተር ብዬ እንዲህ አልኩት፤ «እግዚአብሔር ግን መሰለህ? ወላጆቹን የማይታዘዝ ልጅ ከአሁን በኋላ እንደሚታዘዛቸው ቢነግራቸው ወላጆቹ ሆን ብለው እርሱን ለማሰቃየት የማይችለውን ሥራ እንዲሠራ የሚያዙት ይመስልሃል? እንዲህ ካደረጉ ወላጆች አይደሉም፣ ፈራጆች እንጂ። እነዚህ ሰዎች ወላጆች እንደመሆናቸው መጠን በተለየ ሁኔታ ለልጆቻቸው መሐሪ እንደሚሆኑ ጥርጥር የለኝም። ታዲያ እንዴት ብለህ ነው እግዚአብሔር ሆን ብሎ እንድ ትሰቃይ እንደሚያደርግህ አድርገህ ያሰብከው? አባትህ መሆኑን ረስተሃል?» አልሁት።

ለእግዚአብሔር ራሱን የሰጠ ሰው ብቻ ኃይል እንዳለው ለመግለጽ እወዳለሁ። ለእግዚአብሔር ራሱን የሰጠ ወላጆቹን፣ ሚስቱን፣ ልጆቹን፣ ሥራውን በሕያው አምላክ እጅ ያስቀምጣል። እግዚአብሔር የሰጠውን

ወስጾ ፈጽሞ በዓለም ውስጥ አያኩሣችም። በተቃራኒው ራሱንና ያለውን ሁሉ ለእግዚአብሔር ይሰጣል። ከዚህ ጋር አያይዤ የምናገረው ነገር ያለውን ሁሉ ግለትም ሰዎችን፣ ነገሮችንና እንዲሁም ጉዳዮችን በመለየት በእግዚአብሔር ፊት ለመጣል የሚፈራ ሰው ድል ነሽ ሊሆን አይችልም። ሰውያለውን ሁሉ ለእግዚአብሔር በሰጠ ቁጥር የዚያ ሰው ኃይል ታላቅ ይሆናል። በፈቃዱ ለእግዚአብሔር የሰጠ ሰው ነገሮቹን ሁሉ በእርሱ እጅ ያስቀምጣል። ይህ ብቻ አይደለም፣ አሁንም የበለጠ እንዲወስድ እርሱን ብመጠየቅ ራሱን ለእግዚአብሔር በሞለየት ሕይወቱን ብርቱና ደስተኛ ያደርገዋል። ለእግዚአብሔር ለመስጠት ፈቃደኛ ያልሆነ ሰው ደካማ ነው። እንዲሁም ኃጢአቱኛና ሐዘንተኛ።

8. ያልተናዘዝናቸውን ኃጢአቶች ለመናዘዝ ፈቃደኛ አለመሆን

አንዳንድ ሰዎች ለብዙ ጉዳዮች መፍትሔ አግኝተዋል። ሆኖም በሕ ይወታቸው ኃጢአት መኖሩን ባለመቀበል አይናዘዙም። በመዝ. 66:18 ላይ «በልቤስ በደልን አይቼ ቢሆን» የሚለው ትርጉም ይህ ነው። የሰው ልብ አንድን ኃጢአት መፈለግ ብቻ ሣይሆን ያፈቅራል። በመሆኑም እርሱን ማስወገድ ያቅተዋል። በልብ ይህን ወይም ያንን ኃጢአት በም ስጢር የመውደድ ነገር ይኖራል። በእኛም ዘንድ እርሱን አውጥተን ለመ ናዘዝ ፈቃደኛ አለመሆን ይኖራል። ምንም እንኳ አንድ ሰው አፉን ሞልቶ ኃጢአት ወዳለበት፣ በአጠገቡም አላልፍም ቢልም ልቡ ግን እዚ ያው ነው። ኃጢአት በአብዛኛው የውጭ ባህርይ ጉዳይ ሣይሆን የውስጥ ፍላጐት ነው። በልቡ በደልን የሚያይ ድል ያስፈልገዋል።

ብዙዎች በልባቸው ኃጢአትን መውደድ ብቻ ሣይሆን ያልተናዘዙባ ቸው ኃጢአቶች አሏቸው። እስቲ አንድ ጥያቄ ልጠይቃችሁ፣ ስንት ጊዜ በወንድማችሁ ላይ ኃጢአት አደረጋችሁ? ስለ እርሱ ባሰባችሁ ቁጥር የበደላችሁት መሆኑን ታውቃላችሁ? በልባችሁ ስለ እርሱ ክፉትን ይዛችሁ ውጫዊ ነገራችሁን በመለወጥ ሲወጣ አቅፋችሁ ትስሙታ ላችሁ? ወይም በቤታችሁ በችጋት ትቀበሉታላችሁ? ሰውጫዊ ገጽታ አመለካከታችሁ መለወጣችሁ ያማረ መንገድ እንደሆነ ልገልጽላችሁ እወ ዳለሁ። ነገር ግን ይህ ፈጽሞ የእግዚአብሔር መንገድ አይደለም። የእርሱ

መንገድ ውጫዊ ባህርይን መቀየር አይደለም።እግዚአብሔር የሚጠብቀው ስለ ወንድማችሁ በልባችሁ ውስጥ ክፉ የሆነ የጥላቻ ኃጢአት እንድትናዘዙ ነው።

እዚህ ላይ ከመበዳደል ጋር በተያያዘ መንገድ ታሉ ምን እንደሚል እንይ። ኃጢአትን ስለ መናዘዝ ጉዳይ መጽሐፍ ቅዱስ የግድ በዝርዝር አያስተምርም። ኃጢአትን እንድንናዘዝ ብቻ ያስተምራል እንጂ ዝርዝር ታሪኩን በሌሎች ፊት እንድንተርክ አይደለም። ማቴ. 18:15 «ወንድምህ ቢበድልህ» ይላል። እዚህ ላይ አንድነገር እንመልከት! ወን ድም በብዙ ነገሮች ሊበድል ይችላል። ሊናዘዝ ወደ ተበዳዩ ወንድም ሲቀርብ ግን «ወንድሜ ሆይ በድዬሃለሁ» ማለት ብቻ ይበቃዋል። ያኔም ተበዳዩ ወንድም ይቅር ማለት አለበት ወደ ተበዳይ የመጣው ሰው የተደበቀ ታሪኩን ሁሉ ሊነግረው አያስፈልገውም። ለምን? የሰው ጆሮ ይህን ሁሉ ዝርዝር ሊሰማ የተገባ አይደለምና።

እስቲ ልጠይቃችሁ፣ በልባችሁ ውስጥ ምን ያህል ኃጢአቶች ትመለከታላችሁ? በሕይወታችሁስ እስከ አሁን ድረስ ስንት መተላለፎች አሉ? እንደዚህ ዓይነት ኃጢአቶች ካሉባችሁ ድል ያስፈልጋችኋል። ያለበለዚያ ያለድል ነሽ ሕይወት ልትኖሩ አትችሉም።

ድል ነሽ ሕይወት የሚቻልና አስፈላጊም ነው

ከላይ ለማየት እንደሞከርነው እነዚህ ስምንት ዓይነት ኃጢአቶች ቢኖሩብህ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ሕይወት ለመኖር ድል ያስፈልግሃል። ምናልባት ስምንቱም ዓይነት ኃጢአቶች ላይኖሩብህ ይችላል። ነገር ግን በአንዱ ወይም በሁለቱ ኃጢአቶች ከታሰርህ የኃጢአት ባሪያ ነህ። በሕይወትህ እንዲህ ዓይነት ሁኔታ መኖር የለበትም። ምክንያቱም ምንም ዓይነት ኃጢአት ይሁን ከእግርህ በታች ነው። ድል የማይነሣ ከባድ ፈተና ስለሌለ እንዲሁም ለምንም ዓይነት ኃጢአት እጅ ትሰጥ ዘንድ እግዚአብሔር ለእኛ የሰጠን ኃጢአት ከጌታ በላይ ብርቱ ስላልሆነ ጌታን አመስግን። ሕይወት ከእርሱ ጋር የጠበቀ ግንኙት ያለውና ፈቃዱን የም ናደርግበት፥ እንዲሁም ከተቃራኒ ነገሮች የምንለይበት

ነው። ግንኛውም ክርስቲያን የመንፈስ፣ የሥጋ የአእምሮና የአካል ኃጢ አቶችን ድል መንሣት ይችላል። እግዚአብሔር ይመስገን ይህ የማይገኝ ምናባዊ ሕይወት አይደለም፣ እያየን ያለነው ተግባራዊ ሊሆን የሚችል ሕይወት ነው። የድል ሕይወትን ልንለማመደው የምንችለው ነው።

ድል ለማግኘት ከልብ ግልጽ መሆንና ራስን አለማታለል

ራሣችንን ከማታለል ነፃ እንዲያደርገን እግዚአብሔርን አጥብቀን መለመን አለብን። ምክንያቱም እርሱ የሚባርከው በፊቱ ቅን ልብ ያላቸውንና የማይዋሹትን ሰዎች ሁሉ ነው በታማኝነት «እግዚአብሔር ሆይ በፊትህ ዋሽቻለሁ፣ አውነ ግን ምህረትህን እለምናለሁ» ብትለው ወዲያውኑ ይባርክሃል።

ምናልባት እንዳልረካ ክርስቲያን ያረካህ ዘንድ እግዚአብሔርን ጠይ ቀህ ሊሆን ይችላል። ያልረካ ምንጊዜም የተራብ ሊሆን እንደማይችል በግ ልጽ ልንገርህ። አባካኙ ልጅ የአባቱን ቤት ትቶ ወጣ፤ ያለውንም ሁሉ አጠፋ። በኋላም አሣማዎቹ ከሚበሉት አሠር ሊጠግብ ተመኘ፤ ነገር ግን ማንም አልሰጠውም። ስለሆነም አለመርካት አንድ ነገር ነው፤ አለመ ጥገብ ደግሞ ሌላ ነገር ነው። ዘወትር ደካሞችና ያለማቋረጥ የምንሸነፍ ከሆነ እንዴት ልንረካ እንችላለን? አዎን ላንረካ እንችላለን ግን ከጠዋት እስከ ማታ እንዲህ ያለውን ሕይወት እንኖራለን። በዚህ ምክንያት ዝም ብሎ ካለመርካት መራብ ይሻላል። ምክንያቱም እግዚአብሔር የተራ ቡትን ብቻ ስለሚባርክ አልረካሁም የሚለውን ግን የማርካት ግዴታ የለበትም።

ለብዙ ጊዜ ራሳችንን እያታለልን በእግዚአብሔር ፊት ስለዋሸን ዛሬ ውሸታችንን እናቁም በእርሱ ፊት ሁሉ ነገራችን ግልጥና እርቃኑን ሆኖ የሚታይ መሆኑን እንረዳ። ስለዚህ ከልባችን ግልጽ እንሁን፤ ኃጢአታ ችንን በሰዎች ፊት መናዘዛችን የእግዚአብሔርን ስም ያከብራል። ታማኝ የሆነ ሁሉ በእግዚአብሔር ይጐበኛል፤ ይረካልም።

ምዕራፍ 2

የክርስቲያን ሕይወት በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተገለጠው

«በክርስቶስ በሰማያዊ ሥፍራ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ የባረከን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ» ኤፌ 1:-3

የክርስቲያን የመሸነፍ ልምምድ

በመጀመሪያ ስንድን በእግዚአብሔር ጸጋ ምክንያትልባችን በደስታ ተሞልቶ ነበር። ለሕይወታችን ትልቅ ተስፋ ነበረን። ከአሁን በኋላ ኃጢአቶችን ሁሉ ከእግራችን በታች እንረታግጣለን ብለን አስበን ነበር። በዚያን ጊዜ የትኛውም ፈተና ይሸነፋል፣ የትኛውም ችግር ይፈታል ብለናል። በአጠቃላይ ኃጢአታችን ለመጀመሪያ ጊዜ ይቅር ስለተባለ ደስታ ሰላምን ስለቀመስን የወደፊት ዕድላችን ብሩህ ተስፋ የተሞላ ነበር። ከእግዚአብሔርም ጋር ያለን ግንኙት ድካም የሌለውና ጣፋጭ ነበር። በእውነትና በደስታም ተሞልተን ነበር። መንግሥተ ሰማይም በጣም የቀረበን መስሎ ተሰምቶን ነበር። የማይቻልም ነገር እንደሌለ ያህል ይመስለን ነበር። ዕለት በዕለት ድል ነሽ ሕይወት እንኖራለን ብለንም ሙሉ በሙሉ አምነናል።

በጣም ያሳዝናል እንዲህ ያለው ውብ ልምምድ ብዙም አልቆየም። ጨርሶ ተሸንፈዋል ብለን የቆጠርናቸው ኃጢአቶች ተመልሰው መጡ። አይነኩኝም ያልናቸው ኃጢአቶች ግልብጥ ብለው ተመለሱ፣ የድሮ ንዴትህና ትዕቢትህ፣ ቅናትህም ጭምር። በዚህ ጊዜ መፍትሔ ለማግኘት የእግዚአብሔርን ቃል ብዙ አነበብህ፣ ብዙም ጸለይህ፣ እርዳታ ግን አላገኘህም። ያም ሆኖ በመጀመሪያ የተዳሰስክበትና ከእግዚአብሔር ጋር የነበረህን የቅርብ ግንኙነት አጣህ፣ ስለ ጠፋት ነፍሳት የነበረህ ቅንዓት ቀነሰ፣

ፍቅርህም ቀዘቀዘ፣ ዕለት ተዕለት ሕይወትህም ከድል ይልቅ ብዙ ሽንፈ ቶችን መለማመድ ቀጠልህ፣ በመጨረሻም ትልቅ ጉድለት እንዳለህ ተረዳህ።

በመጀመሪያው ዘመን ከነበሩት ክርስቲያኖች ከነጳውሎስ፣ ጴጥሮስ ዮሐንስ ጋር ራስህን ስታስተያይ ከአንተ ምን ያህል የተለዩ እንደሆኑ አመ ቅህ፣ ይህ ብቻ አይደለም ሌሎችንም መርዳት አልቻልከም። የድል ታሪ ክህን ልትነግራቸው ትችላለህ፣ የመሸነፍ ታሪክህን ግን ደፍረህ አትና ገርም፣ ሁልጊዜም የድል ሕይወትህ አጭር እንደሆንና የመሸነፍ ሕይ ወትህ ግን ረዥም እንደሆነ ይሰማሃል። ከዚህ የተነሣ ዘመንህን በሐዘን ታሳልፋለህ። ይህ ብዙ ክርስቲያኖች የሚጋፉት ልምምድ ነው።

ለንድን ኃጢአታችን ተደምስሷል፣ ዳግሞ አያገኘንም ብለን ገም ተን ነበር። እንዲሁም ያለን ሰላምና ደስታ ለዘለዓለም ከእኛ ጋር ይቆያል ብለን በእውነት አመንን። በአዲሱ የክርስትና ሕይወት ጅምሬ ላይ ይህ አመለካከታችን ትክክል ነው። ታዲያ ኃጢአትና ፈተና ይመለሳሉ ብሎ ማን ይገምታል? ከዳንንስ በኋላ ከብዙ ከፍታ ይልቅ ብዙ ዝቅታ ይኖራል ብሎ ማን ይጠብቃል? በመዳናችንስ ላይ ከደስታ ይልቅ ብዙ ሐዘን ይኖ ራል ብሎ ማን ያልማል? ነገር ግን ፈተና፣ ትዕቢት፣ ቅናት፣ ቶሎ መቆ ጣት ወይም ሌሎች ድክመቶች እንደገና ሲመለሱ በአብዛኛው ሁለት ነገሮች እናደርጋለን። በመጀመሪያ ያለ የሌለንን ኃይል በመጠቀም ኃጢአትን እናሸፍናለን፣ በሁለተኛ ደረጃ ግን ኃጢአትን ፈጽሞ ማሸነፍ አይቻልም የሚል አቋም እንይዛለን።

እነዚህ ኃጢአቶች ከዳንን በኋላ ወደ እኛ ሲመለሱ በአንድ በኩል እነርሱን ለመጫን ብዙ ጥረት እናደርጋለን። ይሕውም በውጭ ተገል ጠው እንዳይታዩብን ነው። በዚህ ጊዜ ኃጢአቱን ለመቆጣጠር ወይም ለመርገጥ የቻለ አማኝ ራሱን እንደ ድል ነሽ ይቆጥራል። በሌላ በኩል ግን በኃጢአት የተሸነፍን ሌሎቻችን የሕይወት ዘመናችንን በማሸነፍና በመሸነፍ ኃጢአትን በመሥራትና በመናዘዝ ከተናዘዝንም በኋላ ኃጢአ ትን በመሥራት እናሳልፋለን። ይህ ዓይነት ልምምድ ተስፋ መቁረጥ ውስጥ ይጥላል። ስለዚህ ኃጢአትን ተቆጣጠርን ቢባል ለጊዜው መጨ ቆን ብቻ ነው የምናደርገው፤ ወይም መጨቆን ካልቻልን ኃጢአት

ሊወገድ የማይችል መሆኑን እናስባለን፤ ቀስ በቀስም ወደ ተስፋ መቁረጥ መዘፈቅና እጅ ወደ መስጠት እንመጣለን።

በግለግለው ጌታ ስም አንድ ጥያቄ ልጠይቃችሁ እፈልጋለሁ። ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ እኛ ወደ መስቀል ሞት ሲሄድ ከዳንን በኋላ ያለን ሕይወታችንን ያየው ዛሬ እንደምንሄድበት ዓይነት አድርጐ ነበር? ኢየሱስ በመስቀል ሲሞት አሁን የምንኖረው ኑሮ ጠዋት ላይ ድሏ፤ ከሰ ዓት በኋላ ላይ ግን ውድቀት እንዲሆን ነው? ሙሉ በሙሉ በመስቀል ላይ የተጠናቀቁው የማዳን ሥራ በቅድስናና በጽድቅ እንድናገለግለው በቂ አይደለም? ጌታ ኢየሱስ ደሙን በመስቀል ላይ ያፈሰሰው የኃጢ አትን ኃይል ሳያይ የገሃነምን ፍርድ በመመልከቱ ብቻ ነው? ወይስ በመስቀል ላይ የፈሰሰው ደም የዛሬውን ስታያችንን ራሳችን እንድንሸከም እርሱ ግን ወደ ፊት ካለው ስቃይ ሊያድነን ብቻ ነው?

ጌታ በቀራንዮ ሁሉን አከናውኗል። አዳኛችን በመስቀል በነበረ ጊዜ ስለ ገሃነም ፍርድ ብቻ ሳይሆን ስለ ኃጢአትም ኃይል አስቧል። እርሱ በኃጢአት ኃይል ያለውን ስቃይና የኃጢአትን ቅጣት ከሩቅ አይቷል። እርሱ ራሱ በምድር ላይ እንደኖረ እኛም በምድር ላይ እንድንኖር የሚያ ስችል ደኅንነት ነው ያለው። በሌላ አገላለጽ በክርስቶስ የመስቀል ሥራና መቤዠት ለመዳን ብቻ ቦታና መብት ያዘጋጀ ሳይሆን ፈጽመን እንድንድን ቦታና መብት ያዘጋጀ ነው። ከአሁን በኋላ አሁን ከምንኖረው የተለየ ሕይወት ልንኖር እንችላለን። ክብር ለበጉ ይሁን! ምክንያቱም ዛሬ የምሥራች ድምጽ ለቅዱሳንም ሆነ ለኃጢአተኞች ስለሰማን ነው።

በእግዚአብሔር የተሰጠ የክርስቲያን ሕይወት

እስቲ ጥያቄ ልጠይቃችሁ፤ ክርስቲያን ምን ዓይነት ሕይወት መኖር አለበት? ይሁ ጥያቄ ለእያንዳንዱ ዳግም ለተወለደ ክርስቲያን ሁሉ እንጂ የበሰሉ ክርስቲያኖችን ብቻ የሚመለከት አይደለም። አንድ ሰው መኖር የሚገባውን ሕይወት ለማወቅ ጉድለቱን መረዳት ይኖርበታል። የዚህን ሕይወት የተለያዩ ገጽታዎች የሚገልጽልን በርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን እንመልከት።

1. ከኃጢአት ነፃ የሆነ ሕይወት

«ልጅም ትወልዳለች፤ እርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና፤ ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ» ማቴ 1:21

በቼርና በፔኪንግ የሚኖሩ አንዳንድ ወንድሞች ኢየሱስን «በፊት ክርስቶስ እያልን እንጠራው ነበር፤ ከአሁን በኋላ ግን ኢየሱስ ክርስቶስ እንላለን፤ እርሱ የተቀባ ብቻ ሳይሆን አዳኛችንም ነው» አሉኝ። ለምን ኢየሱስ ተባለ? ሕዝቡን ሁሉ ከኃጢአታቸው ስለሚያድናቸው ነው። ኢየሱስ ማለት አዳኝ ማለት ነው። ኢየሱስን እንደ አዳኝህ ተቀብለኸው ከሆነ የይቅርታን ጸጋ ላግኝተሃል፤ ይህ እውነት ነው። ለዚህም እግዚአብሔርን ልታመሰግንና ልትባርከ ትችላለህ። ለመሆኑ ኢየሱስ ለአንተ ምን አድርጓል? ጥያቄው አሁንም በኃጢአት ውስጥ ትኖራለህ ወይስ ከኃጢአት ወጥተሃል ነው። «ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና» የሚለው ከእግዚአብሔር የተሰጠና በክርስቶስ የተከናወነ ነው።

የውሃ ዋና መከላከያ ጃኬት ከሕይወት አዳኝ ጀልባ (ላይፍ ቦት) የተለየ ነው። ሰው ባሕር ውስጥ ሲገባ የሚወረወርለትን የሕይወት አድን ጃኬት ይይዛል፤ ስለዚህም አይሰጥምም። በአንጻሩ ግን ከውሃውም አይ ወጣም፤ በሞትና በሕይወት መካከል ይቆያል። የሕይወት አደን ጀልባ (ላይፍ ቦት) ግን ከዚህ ፈጽሞ የተለየ ነገር ነው። በባሕር ውስጥ የወደቀ ሰው ከውሃ ውስጥ ወጥቶ በሕይወት ጀልባ ውስጥ ይቀመጣል። በተመሳሳይ አገላለጽ የጌታችን ማዳን እንደጃኬቱ ሳይሆን እንደጀልባው ሊመሰል ይችላል። ደስ ይበልህ፤ ጌታ በሞት መካከል አይተውህም። ይልቁንም «ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋል» ምክንያቱም በኃጢአታችን አልተወንምና።

በመጽሐፍ ቅዱስ የተነገረው (ደኅንነት) «ከኃጢአታቸው ሁሉ ያድናቸዋልና» የሚል ነው። ያም ሆኖ ግን ምንም በእውነት የዳንን ብንሆንም ስንቶቻችን በኃጢአት እንኖራለን? መጽሐፍ ቅዱስ ሐሰት ሊሆን ይችላልን? በፍጹም! መጽሐፍ ቅዱስ ትክክል፤ ልምዳችን ግን ስህተት ነው።

2. ከእግዚአብሔር ጋር የቀረበ ግንኙት ያለው ሕይወት

«በብላቴናው በዳዊት ቤት የመዳን ቀንድን አስነስቷል... በእርሱም ከጠላቶቻችን እጅ ድነን በዘመናችን ሁሉ ያለ ፍርሃት በቅድስናና በጽድቅ በፊቱ እንድናገለግለው ሰጠን» ሉቃ 1:69–75

እግዚአብሔር በዳዊት ቤት «የመዳንን ቀንድ» አስነስቷል፤ ይህንንም የመዳን ቀንድ በእጃችን አድርገናል። ይህ የመዳን ቀንድ ከጠላቶቻችን ምን ያህል ነፃ አድርጐናል? ከጠላቶቻችንስ ከዳንን ዛሬ ምን ዓይነት ሕይወት ልንኖር ይገባል? ያዳነንን ጌታ አልፎ አልፎ ብቻ በጽድቅና በቅድስና እናገልግለውን? አይደለም! «ዘመናችንን ሁሉ በቅድስናና በጽድቅ» እንድናገለግለው ይገባል። ይህ ነው ከእግዚአብሔር ጋር የቀረበ ግንኙት ያለው ሕይወት።

ይህንን በድፍረት መቀበል አለብን፤ ይኸውም ምንም እንኳ ከጠላቶቻችን እጅ ብንድንም ዘመናችንን ሁሉ «በቅድስናና በጽድቅ» አላገለገልንለትምና ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው ቃል እውነት ከሆነ የግል ልምምዳችን ስህተት መሆን አለበት።

3. ሙሉ በሙሉ በጌታ የረካ ሕይወት

«እኔ ከምሰጠው ውሃ የሚጠጣ ሁሉ ግን ለዘለዓለም አይጠማም፤ እኔ የምሰጠው ውሃ በእርሱ ውስጥ ለዘለዓለም ሕይወት የሚፈልቅ የውሃ ምንጭ ይሆናል እንጂ» ዮሐ 4:14 ብሏል።

ይህ ቃል እንዴት ድንቅ ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተወሰነ ክርስቲያን ወይም ልዩ ጸጋ የተቀበለ ለዘለዓለም የሚፈልቅ የሕይወት ውሃ ይኖረዋል አላለም፤ ጌታ ኢየሱስ ያለው ግንም ነው። በተጨማሪም ቃሉ በቀጥታ የተነገረው ፍጹም እንግዳ ለሆነች ሣምራዊት ነው። እንዲህ አላት። «ብታምኝ ለዘለዓም ሕይወት የሚፈልቅ የሕይወት ውሃ ይኖርሻል» መጠማት ምንድነው? አለመርካት ነው። በጌታ የሚሰጠውን ውሃ የሚጠጣ ግን ዳግመኛ አይጠማም። ከርስቲያን ሁሉ በቃኝን ብቻ ማወቅ ሳይሆን የዘለዓለምን እርካታ ያገኛል። በቃኝን ብቻ የሚያውቅ

ከሆነ ገና ሊያውቅ የሚገባው ነገር ቀርቶታል። እግዚአብሔር ለዘለዓለም እንድንረካ ያደርገናል።

በሻንጋይ፣ በቺንግአንና በሴንሴር የዕቃ መሸጫ መደብሮች አሉ። የከተማውን ዋና መንገድ ይዘው የሚያልፉ ሰዎች ሁሉ ዕቃዎችን እያዩ ይመኛሉ። ይህ ወይም ያ ቢኖረን ሕይወት እንዴት ቆንጆ ይሆን ነበር ብለው ያስባሉ። ይህ መጠማት ነው። የትምህርት ቤት ጓደኛህ ወይም የሥራ ባልደረባህ ያለውን ስትመለከት ለማግኘት ትመኛለህ? ጌታ ግን እንዲህ አለ፤ «እኔ የምሰጠው ውሃ በእርሱ ውስጥ ለዘለዓለም ሕይወት የሚፈልቅ የውሃ ምንጭ ይሆናል እንጂ»። ምንም እንኳ ልምምዳችን የተለየ ታሪክ ቢነግረንም እርሱ የሰጠን ይህንን ዓይነቱን ሕይወት ነው።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እርሱን ማግኘት ብቻ በቂ እንደሆነ ይነግረናል። እኛ ግን እርሱን ማግኘት ብቻ በቂ እንዳልሆነ ነው የምናስበው። አሁንም ሌሎች ነገሮች እንዲያረኩን እንፈልጋለን። ማነው የተሳሳተው? ጌታ የሰጠን ወይስ የእኛ ልምምድ? ከሁለት አንዱ ስህተት መሆን አለበት። በቂ ገንዘብ የሌለው ቸክ አይፈርምም። ጌታ እሰጣለሁ ያለውን ይሰጣል።

ጌታችን በእርሱ የሚያምን ሁሉ ለምን እንደማይጠማ ተናገረ? በዚያ ሰው ሕይወት ውስጥ አንድ አዲስ ነገር ስለሆነ ነው። ይህንን ልጠይቃችሁ፤ ጌታችንን ዕለት በዕለት በቅድስናና በጽድቅ ታገለግሉታላችሁ? የሌሎችን ሰዎች ጥማት የሚያረካ ከአንተ ውስጥ የሚመነጭ ነገር አለ? አለመርካት የሚሰማህ ከሆነ ያለ ምንም ጥርጥር የሕይወት ልምምድህ ስህተት ነው።

4. ኃይል ያለው ሕይወት

«ኢየሱስ ቆሞ– ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣና ይጠጣ፤ በእኔ የሚያምን መጽሐፍ እንዳለ የሕይወት ውሃ ወንዝ ከሆዱ ይፈልቃል ብሎ ጮኸ»። ዮሐ 7:37–38

ከማን ውስጥ ነው የሕይወት ውሃ ወንዝ የሚፈልቀው? በአማኞች ዘንድ ልዩ ክርስቲያን ተብለው ከሚገመቱት ከነጳውሎስ፣ ጴጥሮስና ዮሐንስ ብቻ አይደለም። በኢየሱስ የሚያምን ሁሉ የሕይወት ውሃ ወንዝ

ከሆኑ ይፈልቃል። ከአንተና ከእኔ ግለት ነው። ይህም ከእኛ ጋር የተገናኙ ሰዎች ሁሉ እርካታ እንዲያገኙና ሁለተኛ እንዳይጠሙ ያደርጋቸዋል።

አንዲት ጓደኛ አለችኝ፤ ሰዎች ከእርሷ ጋር ሲገናኙ ወዲያውኑ ዓለምን በመውደዳቸው ራሳቸውን ይወቅሳሉ፤ ትልቅ ቦታ ለመድረስ ያላቸውን የመንጠራራት አሳስፈላጊነት ይረዳሉ። የመመኘትንም ክፉነት ያውቃሉ። እንድ ነገር የሚያረካ ነው ብለህ ታስባለህ፤ ግን አይደለም። ከዚህች እህት ጋር ጥቂት ጊዜ ያሳለፉ በጌታ መርካትን ያገኛሉ። ከእርሷም ጋር በመገናኘታቸው ያ ነገር ምንም እንዳልሆነ ይሰማቸዋል። ኢየሱስ እንዲህ አለ፤ «በእኔ የሚያምን መጽሐፍ እንዳለ የሕይወት ውሃ ወንዝ ከሆኑ ይፈልቃል»። ይህ ጌታ የሰጠን ሕይወት ነው። የሁሉም ክርስቲያን የጋራ ልምምድ መሆን አለበት። እኔ እዚህ የምናገረው የተለዩ ክርስቲያኖችን የሕይወት ልምምድ ሳይሆን ክርስቲያኖች በጋራ ሊለማመዱት የሚገባውን ነው። ራሳችንን ሰዎች እኔን ከተገናኙ በኋላ ጥማት ይናራቸዋልን? ብለን መጠየቅ አለብን። ሰዎች ወደ እኛ መጥተው ሕይወታችን ጉስቋላ፤ አሳዛኝና መፍትሔ ያጣ ነው ሊሉን እኛም በእሽታ ይሁን ብለን መቀበላችን ያሳዝናል። ይህም በበኩሉ የሕይወት ውሃ መሆናችን ቀርቶ እርጥቡን የሚያደርቅ፤ የለመለመውን የሚገድል የተራቆተ ሕይወት ያለን መሆኑን ያሳያል። እንዲህ ያለው ሁኔታ በተሳሳተ ልምምድ ውስጥ መሆናችንን ያረጋግጣል። እግዚአብሔር ግን ተሳስቶ አያውቅም።

5. ከኃጢአት ኃይል ነፃ የሆነ ሕይወት

«ለእናንተ አስቀድሞ እግዚአብሔር ብላቴናውን አስነስቶ እያንዳንዳችሁን ከክፋታችሁ እየመለሰ ይባርካችሁ ዘንድ ሰደደው።» ሐዋ 3:26

ይህን ቃል ጴጥሮስ በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ መመላለሻ ያስተላለፈው መልእክት ነው። ጌታ ኢየሱስ ያከናወነው ሥራ ሰዎችን ከኃጢአታቸው መመለስ ነው። የክርስቲያን የመጀመሪያ ልምምዱ ከኃጢአት ነፃ መሆን ነው። ክርስቲያን ኃጢአትን ሁሉ ድል መንሳት አለበት። እዚህ ላይ የምናውቃቸውን እንጂ የማናውቃቸውን ኃጢአቶች ድል እንድ

ናደርግ አልልም። ለብዙ ዓመታት አስረው የያዙንን ኃጢአቶች ሁሉ ድል መንሳት አለብን። በገላ 6:1 ላይ «ሰው በማንኛውም በደል ስንኳ ቢገኝ» ይላል። በዚህ ዓይነት ሕይወት የሚገኝ እንኳ ቢኖር ድል መንሳት አለበት ምክንያቱም ክርስቶስ ሕይወቱ ነውና። የብዙዎቻችን ልምምድ በአብዛኛው መሸነፍ አልፎ አልፎ ግን ማሸነፍ ነው። እንዴት የተበላሸ ልምምድ ነው።

በሮሜ 6:1–2 ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ ይላል፣ «እንግዲህ ምን እንላለን? ጸጋ እንዲበዛ በኃጢአት እንተን እንኑርን? አይደለም። ለኃጢአት የሞትን እኛ ወደ ፊት እንዴት አድርገን በእርሱ እንኖራለን?»

እኛ በጌታ በኢየሱስ ያመንን ለኃጢአት ሞተናል፤ ስለሆነም ግንም ክርስቲያን በእርሱ (በኃጢአት) መኖር የለበትም። ለኃጢአት መሞታችንን እንዴት እናውቃለን? ጳውሎስ በተከታዩ ጥቅስ መልሱን አስቀምጧል። «ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ የተጠመቅን ሁላችን ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ እንደተጠመቅን አታውቁምን?» ቁ.3 በሌላ አባባል የተጠመቁ ሁሉ ለኃጢአት ሞተዋል ምክንያቱም ጥምቀቱ በጌታ ኢየሱስ ውስጥ ነውና ማለት ነው። ቁ.4 «እንግዲህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሙታን እንደተነሣ እንዲሁ እኛም በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስ፤ ከሞቱ ጋር አንድእንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀብረን።» ይህ ክርስቲያን በየዕለቱ ሊኖረው የሚገባው ዓይነት ሕይወት ነው። የተጠመቁ ሁሉ በአዲስ ሕይወት መመላለስ አለባቸው። ጳውሎስ ይህን መልእክት ሲጽፍ ብአዕምሮው ያሉት አዲስ የተጠመቁ አማኞች እንጂ በሳልና ልዩ ክርስቲያኖች አይደሉም። ሁላችን ተጠምቀናል ስለዚህ በአዲስ ሕይወት መመላለስ አለብን። ይህ ለሁሉም ክርስቲያኖች ከእግዚአብሔር የተሰጠ ልምምድ ነው።

«ኃጢአት አይገዛችሁምና ከጸጋ በታች እንጂ ከሕግ በታች አይደላችሁምና።» ሮሜ 6:14

አ! ይህን ጥቅስ እንዴት እንደምወደው ልንገራችሁ። እስቲ ልጠይቃችሁ፤ ከጸጋ በታች የሆነው ጳውሎስ ነው ወይስ ጴጥሮስ? ወይስ ዮሐንስ? ወይስ ሙሪ? ወይስ ያመኑት ሁሉ? ክርስቶስን አምነው የተጠመቁ ሁሉ ከሕግ በታች ሳይሆኑ ከጸጋ በታች አይደሉምን? ዛሬ ስንቶቻችሁ

ከጸጋ በታች ናችሁ? በረከትና ምስጋና ለእግዚአብሔር ይሁን ሁላችንም ከጸጋ በታች እንጂ ከሕግ በታች አይደለንም። ከላይ የተገለጸውን አባባል የሚገጥመው «ኃጢአት አይገዛችሁም» የሚለው ነው። እዚህ ላይ ኃጢአት ጌታችን መሆን እንደሌለበት ነው ሚናገረው። ድል የተወሰኑ ክርስቲያኖች ልምምድ አይደለም፤ ይልቁንም ሁሉም ክርስቲያኖች የሚጋሩት ልምምድ ነው እንጂ። ምክንያቱም የዳኑ ሁሉ ከጸጋ በታች ናቸውና። በመጀመሪያ ስድን በሮሜ 6:14 ላይ «ኃጢአት አይገዛች ሁምና ከጸጋ በታች እንጂ ከሕግ በታች አይደላችሁምና» የሚለውን ጥቅስ ልዩ ጥቅስ አድርጌ ወሰድኩት። ከዚያም ለብዙ ቀናት በኃጢአት ላይ ድል እንዳለኝ ተናገርኩ። ያም ሆኖ የተቆጣጠረኝ አንድ የተለየ ኃጢአትና ጥቂት ሌሎች ኃጢአቶች ሊረብሹኝ ደግመው ደጋግመው ይመጡ ነበር።

ኃጢአት የሚከተለን ይመስል ለምን ሁልጊዜ እንደሚያጋጥመን አናውቅም። ሆኖም ግን ያጋጥመናል። አንዳንዶች ቶሎ መገንፈል ይከተላቸዋል፤ አንዳንዶችን ትዕቢት ይከተላቸዋል፤ አንዳንዶችን ቅንዓት፤ አንዳንዶችን ከፉ አመል፤ አንዳንዶችን ራስ ወዳድነት፤ ሌሎችን ርካሽ ሐሳብና ያልፀዳ ስሜት ይከተላቸዋል። አንዱን ሰው ሁልጊዜ የሚከተለው የተለየ ኃጢአት አለ። እኔ ራሴ እግሬ ስር የሙጥኝ ብለው የሚከተሉኝ ኃይለኛ ኃጢአቶች ነበሩ። በኋላ ግን ድልን ለማግኘት ኃጢአት በእኔ ላይ ገዥነት ነበረው ብዬ ማመን ነበረብኝ። ከዚያ በኋላ ለጌታ «ኃጢአት አይገዛህም ብለኸኛል፤ ስለዚህ ስህተቱ በአንተ ቃል ላይ ሳይሆን በእኔ እንደሆነ አስግግለሁ» ብዬ ጸለይኩኝ፤ ድልንም መለመመድ ጀመርኩኝ።

የተሸናፊነት ሕይወት ከእግዚአብሔር ያልተሰጠ ሕይወት እንደሆነ ታውቃለህ? እስከ አሁን ድረስ ኃጢአት የሚገዛህ ከሆነ ይህ ከእግዚአብሔር ያልተሰጠህ መሆኑን በግልጽ መረዳት አለብህ። ቅዱስ ቃሉ በግልጽ «ኃጢአት አይገዛችሁም» ይላል።

በሮሜ 8–1 ላይ እንዲህ የሚል ቃል አለ፤ «እንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኩነኔ የለባቸውም»። ኩነኔ የሚለውን ቃል በብዙ መጽሐፍቶቼ ላይ ገልጬዋለሁ። የዛሬ ሃያ ዓመት ገደማ ከመሬት

ተቆፍሮ በወጣ አንድ የድሮ ጽሑፍ ታሉ በአሪጅናል የግሪክ ጽንሰ ልዩ ልዩ ትርጓሜዎች አሉት ከእነኚህ አንዱ «ያለኃይል መሆን» ተብሎ ሊተረጉም ይችላል። በመሆኑም ይህንን ጥቅስ እንዲህ ብለን ልንተረጉመው እንችላለን፣ «እንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ያለኃይል መሆን የለባቸውም» ይህ እንዴት አስደናቂ ነው። እስቲ አንድ ጥያቄ ልጠይቃችሁ፣ ይህ ጥቅስ የማን ነው? የዌስሊይ ብቻ ወይስ የግርቲን ሉተር፣ ወይስ የሀድሰን ቴይለር ብቻ? መጽሐፍ ቅዱስ እዚህ ላይ ምን ይላል? «በክርስቶስ ኢየሱስ ያሉት ከአሁን በኋላ ወይም ከእንግዲህ ያለኃይል አይደሉም» ይላል። እነዚህ ሰዎች እነማን ናቸው? ክርስቲያናች ሁሉ ናቸው። ክርስቲያናች ሁሉ በክርስቶስ ውስጥ እንደሆኑ በክርስቶስ ውስጥ ያለ ማንም ያለ ኃይል ሊሆን አይችልም። በቁጥር 2 ላይ «በክርስቶስ ኢየሱስ ያለው የሕይወት መንፈስ ሕግ ከኃጢአትና ከሞት ሕግ አርነት አውጥቶኛልና» ይላል። አሁንም መቶ ጊዜ ደግሞ እላለሁ፣ ይህ ለተለዩ ቅዱ ሳናች አይደለም። እያንዳንዱ በክርስቶስ ያለ ክርስቲያን ከኃጢአትና ከሞት ሕግ ነፃ ሆኗል። ይህ እውነት ነው።

ያለ «ኃይል» መሆን ምን ማለት ነው? ለዚህ መልስ የሚሆነው በሮሜ 7 ላይ የተነገረው ነው። «ፈቃድ አለኝና፥ መልካሙን ግን ማድረግ የለኝም፤ የማልወደውን ክፉን ነገር አደርጋለሁና። ዳሩ ግን የምወደውን በጎውን ነገር አላደርገውም»። ከቁ. 18–19 በሉላ አነጋገር የሮሜ 7 ጠቅላላ አነጋገር የሚያመለክተው ኃይል የለኝም፤ ማድረግ አልችልም ነው።

የብዙ ክርስቲያናች ታሪክ በውሳኔና ውሳኔን በማፍረስ ሽክርክሪት የተሞላ ነው። ነገር ግን እግዚአብሔርን እናመሰግናለን፣ እንባርካለንም፤ ታሉ ያለአንዳች መሳሳት ማናቸውንም ክርስቲያን ኃይል አልባ እንዳልሆነ ያውጃልናል።

ሕግ ምንድነው?

ሕግ በማናቸውም ቦታና በየትኛውም ሁኔታ በተመሣሣይ መንገድ ይሠራል፤ አንድ ዓይነት ውጤትም ያመጣል፤ የተደጋገመ ልምምድን

ይገልጣል። የማያጸድጥ ክስተትም ነው። ሁልጊዜም በተመጣጣይና በአንድ ዓይነት ውጤት ያበቃል። ለምሳሌ በምድር መሳከል የሰበት ኃይል አለ። አንድን ነገር ስንወረውር በስበት ኃይል ምክንያት የተወረወረው ነገር ሁልጊዜ ወደታች ተሰቦ ይወድቃል። ይህ የሰበት ኃይል የተፈጥሮ ሕግ ነው።

በተመጣጣይ የአንዳንዶች ቶሎ መቆጣት ሕግ ይሆናል። አንዱ ሰው አንድ የሚያስቆጣው ነገር ሲመጣ አንድ ሁለት ጊዜ ፈተናን ይቋቋም ይሆናል። ነገር ግን በሦስተኛውና በአራተኛው ጊዜ ጨርሶ ስሜቱን መቆጣጠር ያቅተዋል። ቁጣው ቶስ በቶስ ገንፍሎ ቦግ ይላል። እንዲህ ዓይነቱ ሰው በተተነኮሰ ጊዜ ይቆጣል፤ ያለ ምንም ለውጥም ሁልጊዜ ተመጣጣይ ውጤት ያስከትላል።

ሰውን ትዕቢት ሁልጊዜ በተመጣጣይ መንገድ ይከተለዋል። በመጀመሪያ በተሞካሸህበት ቃላት እንዳልተነካ ልትሆን ትችላለህ። ሁለተኛውን የማሞካሻ ቃል ስትሰማ ግን ፊትህ በትዕቢት መለወጡ የድግግሞሹ ሥርዓት ተመጣጣይ ውጤት የሚያስከትል ሕግ ይፈጥራል።

ደጋግሚ የምገልፀው ከኃጢአት ሕግ ነፃ የሆኑት የተመረጡ፣ ልዩ የሚባሉ ክርስቲያኖች አይደሉም። ይልቁንም ከአሁን በኋላ ማንም ክርስቲያን ያለ ኃይል አይደለም። የተጠቀሱት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች እውነታዎች እንጂ ትዕዛዝ አይደሉም። ስለዚህ እነርሱ ሁሉ የሁሉም አማኞች ልምምዶች መሆን ይገባቸዋል። የልምምዳችን ከእግዚአብሔር ቃል ጋር አለመጣጣም ምንኛ አሳዛኝ ነው።

6. ሁኔታዎችን ድል የሚነሳ ሕይወት

«ከክርስቶስ ፍቅር ማን ይለየናል? መከራ፥ ወይስ ጭንቀት ወይስ ስደት፥ ወይስ ረሃብ፥ ወይስ ራቁትነት ወይስ ፍርሃት ወይስ ሰይፍ ነውን?... በዚህ ሁሉ ግን በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን።» ሮሜ 8:35–37

በወደደን ጌታ በሁሉ ነገር ከአሸናፊዎች እንድንበልጥ ተደርገናል። ይህ በእርግጥም ማንም ክርስቲያን ሊኖረው የሚገባ ልምምድ ነው። መከራና ሰይፍን ትተን የአንድ ሰው ፊት ትንሽ መለወጥ የክርስቶስን

ፍቅር ምንነት እንድንረሳ ያደርገናል። ነገር ግን ጳውሎስ በእነዚሁ ሁሉ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን ብሎ አወጀ።

ድል የክርስቲያን ጤነኛ ልምምድ መሆን አለበት። እንደ እግዚአ ብሔር ፈቃድ ግንኙውም ክርስቲያን በግናቸውም ዓይነት ሁኔታ ከግሸ ነፍ በላይ መሆን አለበትና መከራ ወይም ጭንቀት ወይም ስደት ወይም ረሃብ ወይም ራቁትነት ወይም ፍርሃት ወይም ሰይፍ ቢሆን ግሸነፍ ብቻ ሳይሆን ከአሸናፊዎች መብለጥ አለበት። የችግር መባባስ ለውጥ አያመ ጣም። ዓለም ክርስቲያኖችን እንደ እብድ ይመለከታቸው ይሆናል። ታዲያ ምንድነው እንደ እብድ ብንቆጠርስ! በክርስቶስ ፍቅር ስለነዚህ ነገሮች ግድ አይሰጠንም! ምክንያቱም ከግሸነፍም በላይ እንሆንባቸዋለ ንና። ከእግዚአብሔር ለክርስቲያን የተሰጠው ሕይወት እንዲህ ያለ ነው። ግን ልምምዳችን ምን ይመስላል? እያዘንኩ እላለሁ እንደ አግባቡ አልኖ ርንም። ባጋጠመን ትንሽ መከራ ምን ያህል ተሰቃየን ብለን እናግር ራለን። ነገር ግን በአግባቡ ብንኖር በእነዚህ ነገሮች ሁሉ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን።

«ነገር ግን በክርስቶስ ሁልጊዜ ድል በመንሳቱ ለሚያዘረን በእኛም በየስፍራው ሁሉ የእውቀቱን ሽታ ለሚገልጥ ለአምላክ ምስጋና ይሁን።» 2ኛ ቆሮ 2:14 የክርስቲያን ሕይወት አንዳንድ ጊዜ የሚሸነፍ፣ አን ዳንድ ጊዜ ደግሞ የሚያሸንፍ አይደለም። ሁልጊዜ ድል የሚነሳ ነው። በመጽሐፍ ቅዱሳዊ መመዘኛ አለማሸነፍ እንደ እንግዳ ነገር የሚቆጠር ሲሆን ግሸነፍ ደግሞ እንደ ተለመደ ነገር የሚቆጠር ነው።

7. መልካም የሆነውን ነገር የሚያደርግ ሕይወት

«እኛ ፍጥረቱ ነንና፣ እንመላለስበት ዘንድ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀውን መልካሙን ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን።» /ኤፌ 2:10/

ይህ ጥቅስ በጣም ከታወቁትና ድንቅ ከሆኑት ከቁጥር 8 እና 9 ጥቅሶች የቀጠለ መሆኑን ሁላችንም እናውቃለን። በቀዳሚዎቹ ጥቅሶች ላይ የተጠቀሰው በጸጋ መዳናችን ነው፤ በቁጥር 10 ላይ ግን እንዲህ ይላል፤ እኛ ፍጥረቱ ነንና እንመላለስበት ዘንድ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀውን መልካሙን ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን።»

ይህ የተወሰኑ ክርስቲያኖች ልዩ መግለጫ አይደለም። ይልቁንም በሁሉ አማኞች ዘንድ የሚደረግ የጋራ ልምምድ ነው፤ ግለትም እግዚአብሔር ሁላችንንም ያዳነን መልካሙን ሥራ እናደርግ ዘንድ ነው።

ጥያቄው፣ እግዚአብሔር ለኛ ባዘጋጀው መሠረት መልካም ሥራ ታደርጋለህ? ወይም በአንድ በኩል መልካም ሥራ እያደረግህ በለላ በኩል ታጉረመርማለህ? ለምሳሌ ወለል ትወለውላለህ እንበል፤ ስትወለ ውል አንተና ሌላው ወንድም ብቻ ይህንን ሥራ እንደምትሠሩ እያሰብህ ታብላላለህ? ሌሎቹ ወንድሞች ለምን እንደ እኔ አይወለውሉም? እያልክ በሃሳብህ ስታወጣ ስታወርድ ወይ በራስህ፣ ወይም ደግሞ በሌሎች ላይ ታንጐራጉራለህ። ይህ መልካም እንደመሥራት ተደርጐ ሊታይ አይች ልም። እያንዳንዱ ክርስቲያን በልቡ ደስ እያለው መልካም ግድረግ አለ በት። በጐ ፈቃድ በማጣት ወይም ጉልበቱን በመቆጠብ ምንም ማድረግ የለበትም። ራስ ወዳድ መሆን የለበትም። ይልቁንም የራሱን ሕይወት እንኳ በሙሉ ፈቃዱ ለሌሎች ማፍሰስ አለበት። ጥሩ ክርስቲያን የሚ ባሉት ብቻ መልካምን ሥራ የሚያደርጉ ከሆነ ነገሩ ምንኛ አሳዛኝ ነው!

8. በብርሃን የተሞላ ሕይወት

«ደግሞም ኢየሱስ– እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ፤ የሚከተለኝ የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ በጨለማ አይመላለስም ብሎ ተናገራቸው።» ዮሐ 8:12

ይህም እግዚአብሔር ለክርስቲያኖች የሰጠው ሕይወት ነው። ለተወሰነ ክርስቲያን ብቻ አይደለም በሕይወት ብርሃን ውስጥ መመላለስ የሚቻለው፣ ክርስቶስን የሚከተሉ ሁሉ በጨለማ መመላለስ የለባቸ ውም። የሕይወት ብርሃን ሊኖራቸው ይገባል። በብርሃን የተሞላ ክርስ ቲያን ጤናማ ክርስቲያን ሲሆን ብርሃን የሌለው ግን ያለ ጥርጥር በሽተኛ ነው፤ ጤናማ አይደለም።

9. ሙሉ በሙሉ የተቀደሰ ሕይወት

«የሰላምም አምላክ ራሱ ሁለንተናችሁን ይቀድስ፤ መንፈሳችሁም፣ ነፍሳችሁም፣ ሥጋችሁም፣ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመጣ ጊዜ ያለ ነቀፋ ፈጽመው ይጠበቁ።» 1ኛ ተሰ 5:23

ይህ ሐዋርያው ጳውሎስ ለተሰሎንቄ አማኞች ያለው ጸሎት ነው። «ሁለንተናችሁን ይቀድስ» በማለት ስለጸለየ ሙሉ በሙሉ መቀደስ የሚቻል መሆኑ ግልጽ ነው። «ፍጹም ያለ ነቀፋ መጠበቅም» የሚቻል ነው። እግዚአብሔር እኛን አማኞችን ፍጹም ሊቀድሰንና ያለ ነቀፋም ሊጠብቀን ይችላል።

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ነገሮች ሁሉ ጌታ ለክርስቲያኖች የሰጠውን ሕይወት ያሳያሉ። «ማዳኑ» አማኞች ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋር ያልተጣረጠ ግንኙት እንዲኖራቸው የሚያደርግና ኃጢአትን ሁሉም ድል አድርገው ከእግራቸው በታች መርገጥ የሚያስችላቸው ነው። ስለዚህ ይህ ጌታ ለእኛ የሰጠው ሕይወት ነው። ይህ ተራ ሐሳብ ሳይሆን የተረጋገጠ ሕይወት ነው።

የእግዚአብሔርን ሙሉ ማዳን መለማመድ አለብን

ዛሬ ልምምድህ ምን ዓይነት ነው? ልምምድህ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ እንደተገለጸው ካልሆነ ሙሉ ደኅንነት ያስፈልግሃል ማለት ነው። መዳንህ እውነት ነው፤ ነገር ግን ደኅንነትን ሙሉ በሙሉ አላገኘህም። ስለዚህ የምሥራች ላሰማህ? ጌታ ኢየሱስ በመስቀል ላይ ያከናወነው ተጋድሎ ከኃጢአት ፍርድ መዳን ብቻ ሳይሆን ከኃጢአት ኃይል አድኖሃል። ይህን ሙሉ ደህንነት ያዘጋጀው ዕለት በዕለት የድል ሕይወት እንድንኖርና የመጀመሪያውንም ደኅንነት እንድናገኝ ነው።

ድል ምንድነው? ድል በእርግጥ የጐደለንን የማሸነፍ ሕይወት የሚያጐናፅፈን ነው። ደኅንነትን ባገኘን ጊዜ ከእግዚአብሔር ሳይሆን ከእኛ በኩል አንድ ነገር ጐድሎ ነበር። እርሱ ውጣ ውረድ የበዛበት ደኅንነት አልሰጠንምና፤ ሙሉ ደኅንነት እንዲኖረን ይፈልጋል። ነገር ግን እኛ

በሚገባ ስላልተለወጥን ዛሬ መፍትሔ አስፈልጐናል። «እርሱም የድል ኑሮ ልምምድ ነው» በድል ኑሮ ደኅንነታችን ሙሉ ይሆናል።

እናንተ በክርስቶስ ኢየሱስ በግመን የዳናችሁ ወገኖቼ! እግዚአብሔር አድኖን መልሶ ደግሞ ኃጢአትና ንስሐ እየተፈራረቁብን እንድን ናር ይፈቅዳልን? የእግዚአብሔር ልጅ ሞቶልን ሳለ በኃጢአት ልንቀጥል እንችላለንን? ከዳንን በኋላ ኃጢአት ሊገዛን ይገባልን? ኃጢአትና እግዚአብሔር ምንኛ እርስበርስ የሚቃረኑ ናቸው! ታዲያ እግዚአብሔር ኃጢአት በእኛ ውስጥ የበላይነት እንዲኖረው ይፈልጋልን? ኧረ በፍጹም! አካላዊም ይሁን ስነ ልቦናዊ ወይም ባህሪያዊ ኃጢአት ኃጢአት ነው።

ጌታን እንዲህ እንበል! «ጌታ ሆይ እባርክሃለሁ! አመሰግንሃለሁም! ምክንያቱም በመስቀል ላይ የሠራኸው ሥራ ከኃጢአት ኃይልና ከቅጣቱም አድኖኛልና! ጉድለቴን አሳየኝና ድልን እንድፈልግ አድርገኝ።» ብለን እንጸልይ። ልምምዳችን መጽሐፍ ቅዱስ ከሚለው ጋር የማይ ስማማ ከሆነ ያለ ጥርጥር ድል ያስፈልገናል። ፍጹም የሆነ ድልነሺ ሕይወት ልናር አልችልም እያልን ራሳችንን አናታል።

ለመሆኑ በክርስቶስ መስቀል ምን ምን ተከናውኗል? ብለን በእውነት እናስባለን? አንዳንዶቻችን የመስቀሉ ተጋድሎ ጥቂት ይሆንብን ይሆናል ብለን እንገምታለን! በዚህም ራሳችንን እንዋሻለን። በእንዲህ ዓይነቱ ሕይወት አንመካ! እንዲህ ዓይነቱ አመለካከት ድልን አይሰጠንም። የክርስቶስ ድል ባህሪው ኃጢአትን ጨርሶ ማስወገድ ነው። ክርስቶስ ሲሞት ኃጢአት ከእግሩ በታች ተረግጧል! ጌታ ይመስገን! ሆኖም ዛሬ ከእግዚአብሔር ጋር ያልተቋረጠ ግንኙነት ያላገኘንና ኃጢአትን ድል ለመንሳት ኃይል የሌለን ድል ያስፈልገናል። ለዚህ እያንዳንዳችንን እግዚአብሔር ይርዳን!

ምዕራፍ 3

የድል ሕይወት ባሕርይ

«የእሥራኤል ኃይል እንደ ሰው የሚጸጸት አይደለምና አይዋሽም አይጸጸትምም አለው።» 1ኛ ሣሙ 15:29

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ድል ለመጀመሪያ ጊዜ በ1ኛ ሣሙ 15: 29 ላይ ተገልጿል። በዚህ ክፍል ላይ ድል (ኃይል) ልምምድ ወይም ከስተት አይደለም። ሰው ነው። እርግጠኛ ነኝ ያ ሰው ግን እንደ ሆነ ሁላችን እናውቀዋለን። እርሱም ክርስቶስ ነው። ስለዚህ ዛሬ እቅ ጩን ልንገ ራችሁ፤ ድል እኛ ዘንድ አይደለም ያለው፤ የኛ ልምምድም አይደለም። እንደ ችግሩ አንተ ድሉም አይደለህም፤ ድል የክርስቶስ ማንኑት (ሰውነት) ለአንተ መኖር ማለት ነው! በዚህ ምክንያት የምና ገኘው ድል አይዋሽም፣ አይጸጸትም። እግዚአብሔር ይመስገን! ድላችን ክርስቶስ ራሱ ነው።

እንደ እግዚአብሔር ቃል የድል ነሽ ሕይወት ገጽታ ባለብዙ መልክ ነው። እኛ ግን ከብዙ ባሕርያቱ አምስቱን እንገልጻለን። የዚህ ሕይወት ትርጉም በጥቂቱ የተለወጠ ሕይወት ብቻ ሳይሆን ይልቁንም ፍፁም የተለወጠ ነው።

ወንድሜ ሆይ! ከሁሉ አስቀድሞ እባክህ ድል ፍፁም የተለወጠ እንጂ ነካ ነካ የተደረገ ሕይወት ብቻ እንዳልሆነ ተረዳ። ድል ማለት ፍፁም ተለወጥሁ ማለት ነው። ገላ 2:20 እንዲህ ይላል፤

«ከክርስቶስ ጋር ተሰቅዬአለሁ። እኔም አሁን ሕያው ሆኜ አልኖ ርም፤ ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል፤ አሁንም በሥጋ የምኖርበት ኑሮ በወ ደደኝና ስለ እኔ ራሱን በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለ እምነት የምኖርው ነው» ይህ ጥቅስ ምን ማለት ነው? አንድ ትርጉም ብቻ አለው። ይኸውም በዚህ ላይ የተነገረው ሕይወት የተለወጠ ሕይወት መሆኑ ነው። ዋናው ነገር «እኔ አይደለሁም ነው።» እኔ ስለ እኔ የሚባል

ነገር ፈጽሞ የለም። መጥፎ እኔ፣ ጥሩ እኔ ወይም ቆሻሻው እኔ፣ ወደ ንጹሕ እኔ የሚለወጥ ነገር አይደለም። ይህ ባጭሩ «እኔ አይደለሁም» ነው። ዛሬ ሰዎች ድል ደረጃ በደረጃ የሚደረስበት ውድቀትም ቀስ በቀስ ወደ ኋላ የሚሄድ ነገር ነው በማለት ትልቅ ስህተት ይፈጽማሉ። አንድ ሰው ስሜቱን መቆጣጠር ከቻለ ወይም ከእግዚአብሔር ጋር የጠበቀ ግንኙት ካደረገ ድል ነሽ ነው እየተባለ ይተረጐማል። ነገር ግን እንዲህ አይደለም። ይህን አንድ ነገር እንያዝ፤ «ድል ከግንነታችን ጋር አንዳች ግንኙነት የለውም።»

አንድ ወንድም እያለቀሰ፣ ድል ሊያደርግ እንዳልቻል መሰከረ፣ እኔም በግልጽ ጨርሶ በልምምዶቹ ኃጢአትን ሊያሸንፍ እንደማይችል ነገርኩት፣ እንዲህም አልኩት፤ እግዚአብሔር አንተ በራስህ ድል እንድትነሳ አንዴም ፈልጐ አያውቅም። ይህ ብቻ አይደለም። ከፉ አመ ልህን ወደ መልካም፣ ሻካራነትህን ወደ ጨዋነት ወይም ሐዘንህን ወደ ደስታ እንድትለውጥ ጨርሶ ጠይቆህ አያውቅም። በቀላሉ የእግዚአ ብሔር መንገድ ሕይወትህን በኢየሱስ ሕይወት እንድትለውጥ ነው። ይህ ከአንተ ጥረት ጋር ምንም ዓይነት ግንኙት የለውም አልኩት።

እንዲሁም አንዲት እህት ለሌሎች ድል መንሣት ቀላል ሆኖ እንደ ሚታይ ለእርሷ ግን እንዲህ ግድረግ በጣም አስቸጋሪ እንደሆነ በምሬት ገለጸች። ስሜቷ ከሌሎች ሰዎች የባሰ መጥፎ ስለሆነ፣ በሐሳቧም ያልፀዳች ስለሆነች፣ በባሕሪዋ ከብዙዎች በላይ ብልጣብልጥ በመሆኗ በምንም ዓይነት ራሷን መቆጣጠር እንደማትችል ተናገረች። የእኔ መልስ እንዲህ የሚል ነበር፤ በእውነቱ ለአንቺ ማሸነፍ ከባድ ሳይሆን አስከማ ይቻል ድረስ በጣም ከባድ ነው። አንቺ ተፈጥሮሽ ከማንም የተሻለ ታማኝ፣ ስሜትሽም ጥሩ፣ ሐሳብሽም ንጹሕ ቢሆን ድል መንሣት ቀላል ሊሆንልሽ እንደሚችል ታስቢያለሽ፤ ነገር ግን እንዲህ ብሎ ነገር የለም። ምክንያቱም ማንኛውም ሰው ምንም ያህል ጨዋና ቅዱስ እንዲሁም ትክ ክለኛ ሰው ቢሆን የራሱን ማንነት ካልለወጠና በምትኩም ክርስቶስ እንዲ ገባ ካልፈቀደ ድል ሊነሣ አይችልም። እንዲሁም ያልተቀደሰና በሁሉም የጐደለ ሰውም ራሱን ከራሱ ሲያስወጣና ክርስቶስን ሲያስገባ ብቻ ድልን ሊለማመድ ይችላል። ክፉ ባሕሪይ ያለውና ሞራሉም ፈጽሞ የተበላሸ

ሰው ደኅንነትን ለማግኘት በኢየሱስ ማመን እንዳለበት እንዲሁም መል ካም ባሕሪ ያለውና ጥሩ ሰውም በኢየሱስ ማመን አለበት። እንደዚሁም ለቅድስና መልካም ባሕሪ ያለውና በሞራሉም መልካም የሆነ ሰው፣ አመለ ጥፉ እንደሆነውና ሞራሉም እንደተበላሸው ድል ያስፈልገዋል ብዬ ነገርኳት።

ድል ክርስቶስ ራሱ ነው። ከእንተና ከእኔ ጥረት ጋር ምንም ግንኙነት የለውም፣ ይህንን እወቅ።

አንድ ጊዜ በሻንጋይ ከፍለ ሀገር ካሉት እህቶች መካከል ድል መን ግት በእጅጉ ያቃታትን አንዲት እህት አገኘሁ። ከልጅነቷ አንስቶ እስከ ሃምሳ ዓመቷ ድረስ ያሳለፈችውን ጉድለቶችና ውድቀቶች ለእኔ ለመንገር ሁለት ሰዓት ፈጀባት። ጌታን ከተቀበለችበት ከልጅነቷ ጊዜ አንስቶ ትዕቢቷንና ነጭናጫነቷን ለመለወጥ ምንም መንገድ አላገኘችም። በየ ጊዜው ጉዳት በሞላበት ሕይወት ትሰቃያለች። እንደ እውነቱ ከሆነ እንደ እርሷ ድል የሚያስፈልገው ሰው ጨርሶ አጋጥሞኝ አያውቅም። በአንጻ ሩም እንደ እርሷ ዓይነት ልዩ የሆነ ድል ያገኘ ሰው አላየሁም። ይህች እህት በውድቀቷ ሁልጊዜ በጣም ታዝን ነበር። እንዲሁም ከነበረባት ጉድለት የተነሣ ራሷን ለማጥፋት አስባለች። ከዚህ ሁሉ ነገር በኋላ ራሷን ረዳት አልባ ሆና እንዳገኘችው ነገረችኝ። ታሪኳን እያጫወተችኝ ሳለ መሳቅ ጀመርኩ። «ዛሬ» አልኳት «ዛሬ ጌታ ኢየሱስ ሊፈውሰው የሚችል እውነተኛ በሽተኛ አግኝቷል!» ብዬ ነገርኳት። ይህቺ እህት ሙሉ በሙሉ በኃጢአቷ ሐሳብ ተውጣ ነበር።

ድል ምን ማለት መሆኑን ካላወቅህ ያስተቀር ስለ ትዕቢቷና መነጫ ነጯ በምትነግርህ ነገር ያለ ጥርጥር ትመረዛለህ፣ ምን አልባትም ለዚህ ተስፋ ላይኖር ይችላል ብለህ ከሷ ጋር ልትስማማ ትችላለህ። ነገር ግን ከእግዚአብሔር ቃል ታላቅ ደስታ የሚል የምስራች ቃለ። ድል መንሣት በአንተ ላይ የተጣለ ቢሆን ኖሮ ምን ጊዜም ድል ማድረግ አትችልም ነበር። ድል ክርስቶስ ስለሆነ ግን ፈጽሞ ችግር የለውም። ጥያቄው በአንተ ሆኖ ድል የሚነሣው ማነው? አንተ ወይስ ክርስቶስ? የሚለው ነው። ክርስቶስ ከሆነ በተፈጥሮህ ምንም ዓይነት ሰው ሁን ችግር

የለውም። ከሌሎች አሥር እጅ የማትረባ ብትሆን እንኳ ክርስቶስ በአንተ ምትክ ከሆነ ድል መንሣት ትችላለህ። ሃሌ ሉያ!

ልጠይቅህ፤ ድል ምንድነው? ድል ክርስቶስ ለአንተ አሸናፊ ሆነ ማለት ነው እንጂ አንተ አሸናፊ ነህ ማለት አይደለም። ቅዱሳት መጻሕፍት አንድ ዓይነት ድልን ብቻ ያስተምራሉ፤ ይኸውም ገላ 2:20 የሚያውጀውን ነው፤ «እኔም አሁን ሕያው ሆኜ አልኖርም ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል።» በደቡብ ቻይና የሚኖሩ ፍክኒዞች «በሞትም ቢሆን መለወጥ የለም» የሚል አባባል አላቸው። ይህን ነገር በፔኪንግ ላሉ ወንድሞች ነገርኳቸው። እኛም በሞትም ቢሆን መለወጥ የለም ማለት አለብን አልኩ። ባለመለወጤ ጌታ የተመሰገነ ይሁን፤ ነገር ግን በእርሱ ተለውጫለሁ!

አንዲት እህት ራስን በመለወጥና በክርስቶስ በመለወጥ መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው? ስትል ጠየቃችኝ። እኔም መልሱን ለመስጠት ተከታዩን ግብራሪያ ተጠቀምኩ፤ ለምሳሌ ያህል እንበል አንድ አሮጌ መጽሐፍ ቅዱስ ይገዛለሁ። ልለውጠው የፈለግሁ ቢሆን አዲስ ሽፋን አለብሰዋለሁ፤ በሙጫም አያይዘዋለሁ፤ በሽፋኑ ላይም በወርቃማ ፊደሎች «መጽሐፍ ቅዱስ» ብዬ እጽፍበታለሁ። በተጨማሪም በገጾቹ ውስጥ የጠፉ ፊደሎች ቢኖሩ በብዕር እጽፍበታለሁ፤ ግልጽ ያልሆነ ፊደል ከተገኘም አደምቀዋለሁ። ይህ ሂደት ግን ምን ያህል ጊዜ እንደ ሚፈጅብኝ አላውቅም። በዚህ ሂደት ስንቱ በትክክል ተሰርቶ እንደ ሚወጣም እርግጠኛ አልሆንም። በአንጻሩ ግን አሮጌውን በአዲስ መጽሐፍ ቅዱስ ለመተካት ብወስን ይህ በሰከንድ ውስጥ ይከናወናል። በዚህ ኛው ሁኔታ አሮጌውን መጽሐፍ ቅዱስ ለመጽሐፍት ሻጩ ሰጥቼ እርሱ በአዲስ ይለውጥልኛል። በመንፈሳዊ ሕይወታችንም እንደዚሁ ነው። እግዚአብሔር ልጁን ለአንተ ስለሰጠ ኃይልህን ማጥፋት የለብህም። በቀላሉ አሮጌውን ሕይወትህን፤ ለእርሱ ስጥ፤ የልጁን ሕይወት በምትኩ ለመቀበል ነው። ይህ በራስ የሚገኝ መለወጥ ሳይሆን በክርስቶስ የሚገኝ ፍፁም ለውጥ ነው።

ሌላ ግብራሪያ ልጠቀም፤ ከብዙ ዓመታት በፊት ለሁለት ዓመታት ዋስትና የተሰጠው አንድ ሰዓት ገዛሁ። ግን እንዲህ ሆነ፤ ሰዓቱ በእኔ እጅ

ከቆየበት ጊዜ ይልቅ ኩባንያው ዘንድ የቆየበት ጊዜ በለጠ። ይሽውም ከገዛሁት ከጥቂት ጊዜ በኋላ በትክክል መቁጠሩን አቆመ። በዚህ የተነሳም ለጥገና ወደ ኩባንያው ብዙ ጊዜ መመላለድ ነበረበት። አንድ ጊዜ፣ ሁለት ጊዜ፣ እስከ አሥር ጊዜ ወደዚያ መሮጡ ሰለቸኝ። ከዚህም በላይ ሰዓቱ እንደተበላሸ ቀረ። ስለዚህም ኩባንያው ሰዓቱን በሌላ ሰዓት ይቀይርልኝ ዘንድ ጠየቅሁት። እነርሱ ግን ይህን የሚፈቅድ የኩባንያ ደምብ ስለሌ ላቸው መለወጥ እንደማይችሉ መልስ ሰጡኝ ነገር ግን ሰዓቱ የሁለት ዓመት ዋስትና ሰላለው በዚህ የዋስትና ጊዜ ውስጥ የጥገና ሥራ እንደ ሚሠሩ ተነገረኝ። ይህ ሁኔታ ለማምንት፣ ለወር ያህል ቀጠለ፣ ሆኖም አልተስተካከለም በመጨረሻም እጅግ ስለሰለቸኝ ሰዓቱን ኩባንያው ዘንድ ትቼው ሄድኩ። ይህ ማብራሪያ የሰው መንገድ ሁልጊዜ የጥገና ሞሆኑ ለማሳየት ያገለግላል። ሕይወት ዋስትና በተሰጠው ዘመን ሁሉ ጥገና፣ ጥገና ጥገና ብቻ ነው። ልመለወጥ ሰው ቆራሁ መንገድ የለውም።

በብሉይ ኪዳን ዘመን ባለው የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክም ቢሆን የእግዚ አብሔር መገሄድ መጠገን ወይም ማደሰ አልነበረም፣ ፍፁም መለወጥ እንጂ። ለምሳሌ ይህን ከፍል አስተውል፣ «እግዚአብሔር ለክብሩ የተከ ላቸው የጽድቅ ዛፎች እንዲባሉ፣ ለጽዮን አልቃሾች፣ አደርግላቸው ዘንድ በአመድ ፈንታ አክሊልን፣ በለቅሶም ፈንታ የደስታን ዘይት፣ በሐ ዘንም መንፈስ ፈንታ የምስጋናን መጐናጸፊያ እስጣቸው ዘንድ ልኮ ኛል።» ኢሳ 61፡3 መተካት የእግዚአብሔር መንገድ ነው። አመዱ አይለወጥም፣ ይልቁንም በምትኩ በአመዱ ፈንታ አክሊልን ይሰጣል እንጂ ወይም ለቅሶን የማሻሻል ሥራ አይሠራም። ለልቅሶ የደስታን ዘይት ይሰጣል እንጂ እንዲሁም በሐዘን መንፈስ ፈንታ የምስጋና መጐና ጸፊያ ይሰጣል። ማሻሻል የእግዚአብሔር መንገድ አይደለም። ምንጊዜም የእርሱ መንገድ መለወጥ ነው።

ባለፍኩባቸው ዓመታት ሁሉ ራሴን መለወጥ አልቻልኩም። ነገር ግን እግዚአብሔር ለዋውጦኛል። ይህ ቅድስና ነው፣ ይህ ፍጹምነት ነው፣ ይህ ድል ነው፣ ይህ የእግዚአብሔር ልጅ ሕይወት ነው። ከዚህ በኋላ የክ ርስቶስ ጨዋነት የእኔ ጨዋነት ነው፣ የክርስቶስ ቅድስና የእኔ ቅድስና ነው፣ የክርስቶስ የጸሎት ሕይወት የእኔ የጸሎት ሕይወት ነው፣

የክርስቶስና የእግዚአብሔር ግንኙት የአኗኗር ግንኙት ነው። ድል የማል ነገው ከባድ የሚባል ኃጢአት የለም፣ የማሸንፈው ኃይለኛ ፈተና የለም፣ ምክንያቱም ድል የሚነግው የክርስቶስ ሕይወት እንጂ እኔ አይደ ለሁምና ነው። አስቲ አንድ ጥያቄ ልጠይቅህ፣ ክርስቶስ ትልቅ ኃጢ አትን ሊፈራ ይችላልን? ለትልቅ ፈተናስ ይንበረከካልን? እሩ በፍጹም! እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን፣ ከአሁን በኋላ አልፈራም ምክንያቱም ከዚህ በኋላ ክርስቶስ እንጂ እኔ አይደለሁምና።

የዚህ ሕይወት መርህ ስጦታ እንጂ ዋጋ አይደለም

በዚህ ሁሉ አንድ ልንገነዘበው የሚገባ ነገር አለ፣ ይኸውም ድል ነፃ ስጦታ እንጂ የሥራ ዋጋ አለመሆኑን ነው። ስጦታ ምንድነው? በሥራ የምታገኘው ደሞዝ (ዋጋ) አይደለም። በጸጋው ከተተባበ የሚሿላ ነገር እንዲኖር ሳያስፈልግ እንዲው በነጻ የሚሰጥ ነገር ነው። እንዲሁ የድል ነሽ ሕይወት የአገኑን ጥረት የማይጠይቅ ነፃ ስጦታ ነው። ፃሌ ሉያ! «በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ድል መንሣትን ለሚሰጠን ለእግ ዚአብሔር ምስጋና ይሁን» /1ኛ ቆሮ 15:57/ ድል እግዚአብሔር ለእኛ ሊሰጠን ያዘጋጀው ነገር ነው። የእኛ ድል በግል ጥረት የተገኘ ሳይሆን በነፃ የተገኘ ነው።

ብዙውን ጊዜ አማኞች እጅግ የተሳሳተ አስተሳሰብ አለን፣ ይኸውም ደኅንነትን በነፃ አገኘን እያልን ድል መንሣትን ግን በእኛው በራሳችን ይገኛል እንላለን። ደኅንነትን ለማግኘት መልካም ሥራ እንደማንጨ ምር እናውቃለን። በቀላሉ ወደ መስቀሉ መጥተን ጌታ ኢየሱስ እንደ ግል አዳኛችን መቀበል ነው፣ ወንጌል ይሄ ነው። በሥራ እንደማንድን እናው ቃለን። ነገር ግን ከዳንን በኋላ ለመቀደስ በዘጉ ሥራችን መተማመን እንዳለብን እናስባለን። ይህም በሥራህ መዳን ባትችልም ድል ለመንሣት በሥራህ መተማመን አለብህ እንደማለት ነው።

ቁርጥ ያለ አንድ ነገር ልንገርህ፣ በሥራህ እንዳልዳንህ ሁሉ በሥራ ህም ድል መንሣት አትችልም። መልካም ግድረግ እንደማትችል እግዚአ ብሔር ተናግሯል። ክርስቶስ ስላንተ በመስቀል ላይ ሞቶአል፣ አሁንም

በውስጥህ ለአንተ ይናገራል። ከሥጋ የሆነ ሥጋ ነው። ከእርሱ የሚመጣውን ሁሉ እግዚአብሔር ፈጽሞ አይቀበለውም፤ ያም ሆኖ ደህንነት በክርስቶስ መስቀል ላይ ያለቀ መሆኑን እያወቅን በሕይወታችን ድል ለማግኘት መልካም ለመሥራት ግሰብና መልካም ነገሮችን ማድረግ አለብን እንላለን። አንድ ነገር በደምብ እንረዳ ምንም መልካም ነገር በራሳችን ማድረግ አንችልም። ድል ከእግዚአብሔር በነፃ የሚሰጥ ስጦታ ነው።

ከ1ኛ ቆሮ 15:57 በፊት ያለው ጥቅስ ስለ ኃጢአትና ሞት ይናገርና በቁጥር 57 ላይ እግዚአብሔር ስለ ሰጠን ድል ያመራል። ድል ግልት በሞት እንዲሁም በሕማና በኃጢአት ላይ ባለውጤት መሆን ማለት ነው። እግዚአብሔር የፈጸመው ቤዛነት ኃጢአትን ብቻ ሳይሆን ሕማንና ሞትንም ድል ይነሣል። በመከከላችሁ ሆኜ ለእያንዳንዳችሁ ተራ በተራ እግዚአብሔር ድልን ለማን ሰጥቷል የሚለውን ወንጌል ብነግራችሁ ምንኛ ደስ ባለኝ ነበር።

እንዴት ብዬ ነው ፈተናን የማሸንፈው? ትዕቢቴንስ እንዴት አስወግደዋለሁ? ቀናተኛነቴንስ እንዴት ድል እመታዋለሁ? ብላችሁ እንደምታስቡና በዚህ ነገር ጌታችንን እንደምትጠይቁ ጥርጥር የለኝም። ኃጢአት ኃይሉን በአናንተ ላይ በገለጸ ጊዜ ከኦጢአት ለመዳን ጌታን ምንኛ ጠራችሁ? ያም ሆኖ ግን ተስፋ ቢል መቁረጥ ምን ያህል ድል እስከምታገኙ ቆማችሁ ይሆን? ዛሬ ግን አንድ የምንገራችሁ የምስራች አለ! አሁም ይኸ ነው፤ በጌታ ኢየሱስ ያለው ገርነት፤ ቅድስናና የጸሎት ሕይወት ጌታን እንደገል አዳኛችሁ ከተቀበላችሁበት ጊዜ ጀምሮ በነፃ ተሰጥቷችኋል። በክርስቶስ ያመንክ ወንድሜ ሆይ ጌታን ስትቀበለው የእርሱ የሆነው ሁሉ የአንተ ነው። ይህ የምስራች ካልሆነ እንግዲያውስ የምስራች ምንድነው?

ከፈለግህ መጽሐፍ ቅድስን ለማንበብና ከእግዚአብሔር ጋር ያልተቋረጠ ሕንኙነት ለማድረግ ምን ያህል ሰዓትና ኃይል እንዳጠፋህ አስላ። እንዲሁም ኃጢአትንና ቶሎ መናደድን ለማሸነፍ ምን ያህል ጥረት እንዳደረግህ እውጣና አውርድ። በዚህ ሁሉ ግን ኃጢአትን ካለማድረግ ይልቅ ኃጢአትህን መናዘዝ ትችል ይሆናል። ቢሆንም በአብዛኛው ኃጢአትን ካለማድረግ ልትቆጠብ አልቻልክም። ስለዚህ ባለማቋረጥ ትሸነፋለህ።

ይህንንም ልታስወግድ ጥረት ብታደርግ መዋሸትህን ትቀጥላለህ፤ በዚህም ተስፋ ትቆርጣለህ። በአንድ ወቅት አንድ ቦታ ሳገለግል ላለመዋሸት ቢሞክሩም ከመዋሸት ግን ራሳቸውን ሊለውጡ ያልቻሉ መሆናቸውን የነገሩኝ በርካታ ወንድሞችና እህቶች አጋጥመውኛል። በእውነት ዛሬ የምስራችን የሚያበስር ወንጌል ለአንተ አለኝ! እግዚአብሔር የጌታ ኢየሱስን ቅድስና፣ ትዕግሥት፣ ፍጹም ፍቅርና ታማኝነት በነፃ ሰጥቶሃል! ለሚፈልግ ሁሉም በነፃ ሰጥቷል። በኢየሱስ እንዳለው የተቀደሰ ኑሮ ውበት ያለው የቀረበ ሕብረት እግዚአብሔር ከራሱ ጋር ሰጥቶሃል። በራሴ አሸንፋለሁ ብለህ የምትንጠራራ ከሆነ ግን ከሃያ ዓመት ድካምና ጥረት በኋላም ክፉ ዓመልህን ወይም ትዕቢትህን ልትለውተ አትችልም። ከሃያ ዓመት በፊት እንደነበርኸው ሆነህ ትቀራለህ።

እግዚአብሔር ለአንተ ፍጹም ደኅንነት አለው። የክርስቶስ ትዕግሥትና ቅድስና የአንተ እንደሆነ ሁሉ እግዚአብሔር የክርስቶስን መልካም ነገር ሁሉ የአንተ እንዲሆን አድርጓል። ይህ ነው እግዚአብሔር የሰጠን ደኅንነት ፡

በሥራ ራሱን ሊያድን የሞከረ ኃጢአተኛ አይተህ ታውቃለህ? እኔ ጥቂቶች አጋጥመውኛል። እንዲህ ዓይነት ሰዎችን ስታገኛ «ክርስቶስ ሁሉን ስላደረገ አንተ ለደኅንነት ምንም ዓይነት መልካም ነገር መፈጸም (መሥራት) አያስፈልግህም፤ እግዚአብሔር እንድትድን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ስለሰጠህ ማድረግ ያለብህ እሱን መቀበል ነው።» ብለህ ትነገረዋልህ። በተመሳሳይም ድልን በሚመለከት «ክርስቶስ ሁሉን ስላደረገው አንተ ምንም ማድረግ አያስፈልግህም። ደኅንነት ያለ አንተ ሥራ ከእግዚአብሔር ነፃ ጸጋ እንደተገኘ ሁሉ በኃጢአት ላይ ድልም ያለ አንተ ሥራ የእግዚአብሔር መልካም ስጦታ ነው። ደኅንነት የአንተን ጥረት አይሻም፤ ድልም እንዲሁ ጥረትህ አያሻውም። ለምሳሌ መጽሐፍ ቅዱስ ለአንተ መስጠት ብፈልግ በመጀመሪያ ማወቅ ያለብህ ነገር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጻፉት ቃላት የአንተ አይደሉም፣ ሽፋኑም በአንተ አልተሸፈነም፣ ርዕሱም በወርቃማ ፊደሎች በአንተ አልተጻፈም። እነዚህ ሁሉ በሌሎች የተደረጉ ናቸው። ይህን እንደ ስጦታ ብሰጥህ አንተ ያልደከምህበትን ነው ያገኘኸው። የድልም ነገር እንደዚሁ ነው። እግዚአብሔር

በነፃ የሚሰጥህ ስጦታ ስለሆነ ወደ ድል፣ ቅድስናና ፍፁምነት በራሳችን ጥረትና ሥራ ቀስ በቀስ አንመጣም፤ በፍጹም እንደዚህ አይቻልም። ግንም ድል የነፃ ቢኖር ድሉ በጌታ ኢየሱስ የተገኘ ነው።

ትዕቢቷንና ቁጡነቷን ለማስወገድ ከሃያ ዓመት በላይ ሞክራ ሳይሳካላት መቅረቱ ብቻ ሳይሆን ፍጹም የተስፋ መቁረጥ ስሜት የተሰማት አንዲት እህት ለምክር አገልግሎት ወደ እኔ መጣች። የመከርኳትም እንዲህ ብዬ ነበር፤ «ትዕቢትንና ቁጡነትሽን አስወግዳለሁ ብለሽ የምትጥሪ ከሆነ ሌላ ሃያ ዓመት ቢጨመርም አይሆንልሽም። «የእግዚአብሔርን ስጦታ» ከተቀበልሽ ግን ዛሬውኑ ከኃጢአትሽ ነፃ ትሆኛለሽ። ይህ ስጦታ በራሱ በእግዚአብሔር የተሰጠ ነፃ ስጦታ ነው፤ እሱም ክርስቶስ ኢየሱስ ነው። ኢየሱስን አዳኝሽ አድርገሽ እንደተቀበልሽው የድልሽም መሪ አድርገሽ ብትቀበይው ድል ይኖርሻል።» ብዬ መከርኳት። ይህን እንደሰማች እግዚአብሔር የሰጣትን ይህንን ድል ኢየሱስን ድሏ በማድረግ በእምነት ተቀበለች። እስቲ የሥራህን ከንቱነትና በሕይወትህም ያጋጠመህን ውድቀት ተገንዘብ።

በሮሜ 6፡14 ላይ «ኃጢአት አይገዛችሁምና፣ ከጸጋ በታች እንጂ ከሕግ በታች አይደላችሁምና» ይላል። አሁንም ይህን ጥቅስ እስቲ ደግመን እንየው። ለምንድነው አማኞችን ኃጢአት የማይገዛን? ከሕግ በታች ሳይሆን ከጸጋ በታች ስለሆንን ነው። መልሱ ይህ ከሆነ ከሕግ በታች መሆን ማለት ምን ማለት ነው? ምንም እንኳ ደጋግሜ ብገልጸውም ከሕግ በታች የሚለው አባባል ሰው በእግዚአብሔር ፊት በድካሙና በጥረቱ እንዲመላለስ መጠየቁን ያመለክታል። እንዲህ ከሆነ ከጸጋ በታች መሆን ማለትስ ምን ማለት ነው? ከጸጋ በታች መሆን እግዚአብሔር ስለ ሰው መሥራቱን ያመለክታል። እንግዲህ በእግዚአብሔር ፊት በጥረታችን እንገኝ ካልን ኃጢአት ይገዛናል፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ስለ እኛ በጸጋው ከሠራ ኃጢአት በእኛ ላይ ጌትነት አይኖረውም። እግዚአብሔር ስለ እኛ ሲሠራ ኃጢአት አይገዛንም። እንግዲህ የእኛን ጥረት የሚጠይቅ ሁሉ ድል አይደለም። ኃጢአትን ለማሸነፍ የምናደርገውን ትግል ስናቆም እግዚአብሔር ስለ እኛ እየሠራ ድል በነፃ ወደ እኛ ይመጣል።

እንበል ክርስቲያን የሚለውን መጠሪያ ስም እስከታጣ ድረስ ኃጢ አት ያሸንፈህ ሰው ትሆናለህ። ልንገርህ ይህንን የእግዚአብሔርን ስጦታ አሁን ብትቀበል ወዲያውኑ የድል ሰው ትሆናለህ። የድል ማርህ የስጦታ መርህ ነው፤ የሥራ ዋጋ ግን አይደለም። ይህን የእግዚአብሔር ስጦታ በመቀበልህ ሕይወትህ ባለ ድል ይሆናል። ሁሉም ይስተካከላል።

የድል ሕይወት በስጦታ እንጂ በጥረት የሚገኝ አይደለም።

የድል ሕይወት የሚገኘው በነፃ እንጂ በጥረት አይደለም። በነፃ ማግኘ ትና በጥረት ማግኘት መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው? በነፃ ማግኘት ማለት አንድን ነገር ያለ ጥረት ማግኘት ሲሆን በጥረት ማግኘት ደግሞ ቀስ በቀስ ብዙ ነገር አድርገህ ወደ አለምከው ግብ ለመድረስ በውጣ ውረድ የምትሠራው ሥራ ማለት ነው። የክርስቲያን ድል ግን ቀስ በቀስ የሚደረስበት ጉዳይ አይደለም።

በአንድ ወቅት ወደ ኪሊንግ ተራራ እወጣ ነበር። በጌታ ወንድም የሆነ ሲንግ ሊያንግ ዮ፤ ከእርሱ ጋር ተራራውን እንድወጣ ጠየቀኝ። ያንን ረጅም ተራራ እየወጣን ሳለ በዚያው ልክ እየደከመኝ መጣ። የተወ ሰነ ርቀት እንደሸፈንን ወንድም ዮን ከዚህ በኋላ ምን ያህል እንጓዝለን ብሎ ጠየቅሁት። ከተራራው ጫፍ ለመድረስ ምንም ያህል አልቀረንም ብሎ መለሰልኝ። ቀስ እያልን መውጣቱን ተያያዝነው፤ ያም ሆኖ ግን አሁንም አልደረስንም። ወንድም ዮን በጠየቅሁት ቁጥር በመደጋገም የሚ ሰጠኝ መልስ አሁን ትንሽ ነው የቀረን የሚል መልስ ነበር። በመጨረሻም ግን በወላንሳ ይዘውኝ ወደ ተራራው ጫፍ ከወጣን በኋላ ኪሊንግን አገኘሁት። እዚህ ላይ ልነግራችሁ የምፈልገው የእኛ ነገር በድካም ነው የሚገኘው፤ ከጌታ ዘንድ የምንቀበላቸው ድሎች ሁሉ ግን ያለምንም ውጣውረድ የሚገኙ ናቸው።

«በአንዱም በደል ሞት በአንዱ በኩል ከነገሠ ይልቁን፥ የጸጋን ብዛ ትና የጽድቅን ብዛት ስጦታ ብዛት የሚቀበሉ በአንዱ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በሕይወት ይነግሣሉ።» ሮሜ 5:17

በዚህ ጥቅስ ላይ ጳውሎስ ድል ስጦታ ነው በግለት ይናገራል። ስለ ዚህ ድል ቀስ በቀስ የምታገኘው ነገር ሳይሆን የተሰጠህ ስጦታ ነው። ድልን ለማግኘት የምታደርገውን እንቅስቃሴ አቁም። የአንተን ሥራ አይ ጠይቅም። ለምሳሌ መጽሐፍ ቅዱሴን ልሰጥህ ፈለግሁ። ለመቀበል ጥረት ማድረግ አለብህ እንዴ? በፍጹም። እጅህን ትዘረጋለህ፥ በስኮንድ ውስጥ ታገኘዋለህ። ስጦታ እንደመሆኑ መጠን እቤትህ ገብተህ መጸም እንዲ ሁም በቀን ሦስት ጊዜም ፊትህን ወደ ኢየሩሳሌም አዙረህ ተንበርክከህ መጸለይ የለብህም። ይህ ሁሉ አስፈላጊ አይደለም። ከአንተ የሚጠበቀው መቀበል ብቻ ነው። መጽሐፍ ቅዱስን ለመቀበል ምን ዓይነት ሥነ ሥር ዓት መፈጸም ያስፈልጋል? በእጅህ መቀበል እንጂ ምንም ዓይነት ሥነ ሥርዓት አያስፈገውም። ድልም እንዲሁ ነው። በነፃ የምታገኘው ስጦታ እንጂ በጥረት የምታገኘው አይደለም።

«ከእግዚአብሔር ዘንድ ጥበብና ጽድቅ ቅድስናም ቤዛነትም በተደረ ገልን በክርስቶስ ኢየሱስ የሆናችሁ ከእርሱ ነው።» 1ኛ ቆሮ 1:30 ሁላችንም ይህን ጥቅስ በሚገባ እናውቀዋለን። እዚህ ላይ ስለ ጥበብ አጠ ቃላይ ሐሳብ ምንም መናገር አያስፈልገኝም። እንዲሁ አልፈዋለሁ። ነገር ግን ጽድቅ፣ ቅድስና ቤዛነት በሚለው ላይ እናተኩር እስቲ አሁንም በድጋሚ ልጠይቃችሁ፤ እግዚአብሔር ክርስቶስን «ቅድስናችን» ያደረ ገው መቼ ነው? ክርስቶስ በመስቀል ላይ ከሞተበት ጊዜ ጀምሮና እር ሱን አዳኛችሁ አድርጋችሁ በእምነት ከተቀበላችሁበት ጊዜ አንስቶ እን ደሆነ በእርግጠኝነት ትመልሱልኛላችሁ። እርሱን እንደ ጽድቃችሁ ከመ ቀበላችሁ በፊት ሦስት ቀን ግልቀስ አላስፈለጋችሁም፤ እንዲሁም ያስቀ የማችኋቸውን ሰዎች ይቅርታ መጠየቅም አላስፈለጋችሁም፤ እግዚአብ ሔር የተመሰገን ይሁን! የእግዚአብሔር ልጅ ስለ እያንዳንዳችን ሞቷል፤ በእምነት ጽድቅን ብቻ ሳይሆን ቅድስናንም ተቀብለሃል። ጌታ ኢየሱስን እንደ ፅድቅህ አድርገህ እንደተቀበልኸው ሁሉ እንደ ቅድስናህም አድ ርገህ በመቀበሉ ጉዳይ ላይ መቸገርህ ነው። ስለዚህም አብዛኛውን ጊዜ ኃይልህን በማጥፋት በራስህ ዙሪያ ትዞራለህ። በክርስትና መንገድ ቀስ በቀስ ተጉዞ አንድ ቀን ቅድስናን አገኛለሁ ብለህ ካቀድህ ዘበት ነው፤ መቼም አታገኝም። የራሱን ጽድቅ ለመፈጸም የሚያስብ ሁሉ

እንደማይድን በተመሳሳይ ቅድስናን አገኛለሁ ብሎ የሚያስብም በምንም ዓይነት ባለ ድል አይሆንም።

በነፃ በመቀበልና በጥረት በማግኘት መካከል ያለው ልዩነት ምንድ ነው? የጊዜ ልዩነትን እናያለን። አንዱ ወዲያውኑ የሚከናወን ሲሆን ሌላው ደረጃ በደረጃ የሚገኝ ነገር ነው። አንድ የዶሮ ሌባ በሳምንት ሰባት ዶሮ ይሰርቅ ነበር። በኋላ ላይ ግን ይህን ባሕሪውን ለመልወጥ አሰበ። ከስድስት ሳምንት በኋላ ጨርሶ መስረቅን ለማቆም በማሰብ በየሳ ምንቱ አንዳንድ ዶሮ እየቀነሰ መስረቅ ጀመረ ይባላል። ይህ ታሪክ እውነ ትነት ሊኖረው ይችላል። የጌታ ድል ግን ወዲያውኑ የሚገኝ ነው።

ቼር በነበርኩ ጊዜ ቁጣው በጣም አስደንጋጭ የሆነ አንድ ወንድም አገኘሁ። ቁጣው ሲገነፍል ሚስቱና ልጆቹ ይርበደበዳሉ። በልብስ ጥልፍ ሥራ ሱቁ ውስጥ ያሉ ሠራተኞች፣ ከርስቲያን ወንድሞች እንኳ ይፈሩና ይንቀጠቀጡ ነበር። አንዳንዴም በስብሰባ ስፍራዎች ሁሉ ሁከት ይፈጥር ስለነበር አንድ ቀን ይህን ስሜቱን ለመቆጣጠር ምንም መንገድ እንዳላገኘ ነገረኝ። እኔም ጌታን እንደ ድሉ ቢቀበል ወዲያውኑ ድል ሊያገኝ እንደ ሚችል ነገርኩት። ወዲያውም ተቀበለ! ድልንም መለማመድ ጀመረ።

ጥቂት ከቆየ በኋላ ድል ማግኘት ከጀመረ ምን ያህል ጊዜ እንደሆነው ጠየቀኝ ቀኑን አብረን ስንቆጥር አንድ ወር ገደማ ሆኖታል። በዚህ ጊዜ ውስጥ አንድ ቀን ሚስቱ ለሞት እስክምትደርስ በጣም ታማ እንደነበረ ነገረኝ። እንዲህ ያለው ነገር በፊት ቢከሰት ኖሮ በጣም ተጨንቆ ፊቱን በማጨማደድ እየተብሰጨ ከአንዱ ክፍል ወደ ሌላው ይወጣና ይገባ እንደ ነበር አጫወተኝ። በዚህ ጊዜ ግን ሚስቱ ስትታመምና የልብ ትርታዋ ሲቀንስ የእግዚአብሔር ፈቃድ ይሁን እንዳለ በተረጋጋ ስሜት በለስላሳ መንፈስ ነገረኝ። አስፈሪ ቁጣው ፈጽሞ ተወገደ። ሚስቱም ታክማ ተሻላት እርሱም የሚቻለውን ሁሉ በማድረግ ይጠነቀቅላት ነበር።

ቼርን ትቼ ስሄድ ሊሸኘኝ መጣ። ባለፉት ጊዜያት የሌላ ሰው እንጂ የሱ የራሱ ሚስት ያልታመመች ያህል ምንም ዓይነት ጭንቀት እንዳልነበ ረበት አጫወተኝ። በዚህም ጊዜ በሱቁ ውስጥ የጥልፍ ሥራ የሚሠሩ ሴት ሰራተኞቹ ለቁጥጥር በጣም አስቸጋሪዎች ነበሩ። በተጨማሪም ባለ ፈው ወር በሱቁ ውስጥ ብዙ አሳዛኝ ነገሮች የተፈጸሙ መሆኑን ነገረኝ።

ቀድሞ ቢሆን በጣም ይበሳጭ ነበር። አሁን ግን የእርሱ ችግሮች እንዳል ሆኑ አድርጉ ወሰዳቸው። ቁጣው ስለጠፋ እንዲያውም እየሳቀ ለምን እን ዲህ ያለ ነገር ያደርጋሉ ማለት ጀመረ። ይህ ድል ስጦታ ነው። በጥረት የማግኘት ነገር ቢሆን ናሮ ከሃያ ዓመታትም ጥረት በኋላ ድል አይቀ ዳጅም ነበር።

አንድ ጊዜ አንዲት ሚሲዮናዊት ወደ ሕንድ ሄደች። በጉዞዋ ክፉ አመሏን እንጂ ከእሷ ጋር ምንም ነገር ይዛ አልሄደችም ነበር። ይህች ሚሲዮናዊት እህት ሁልጊዜ ትናደዳለች። መንፈሳዊ ጓደኛዋ እሷ መታ ገስ ከቻለች መላው ዓለም መታገስ ይችላል ስትል መስክራለች። የድል ሕይወትን ምስጢር ታውቅ ስለነበርም ለዚህች ሚሲዮናዊት ይህ ህይወት እንዴት እንደሚገኝ በደብዳቤ ነገረቻት። ይህች ሚሲዮናዊት ደብዳቤ ውን ተቀብላ እንደሚለው አደረገች። ከሦስት ወር በኋላም ከሚሲዮናዊቷ የመጣው የመልስ ደብዳቤ ዋና ሐሳቡ ይኸ ነበር፤ «ደብዳቤሽን እንዳነብ ብኩ ወንጌል ይህ እንደሆነ አወቅኩ! ክርስቶስ ትዕግሥት ነው፤ እርሱን የእኔ ድል አድርጌ በተቀበልኩት ጊዜ ብስጭት በነነ። በቅርብ ጊዜ ባጋጠ ሙኝ ከባድ ውድቀቶች ምክንያት ግን ለሦስት ወር ያህል ሃሳብሽን እስካ ጣጥመው ድረስ ለመናገር አልደፈርኩም። እነዚህ ሕንዳውያን አገልጋ ዮች ዝግተኞችና ድብቆች ናቸው። የቤቴን መዝጊያ በዘጋሁ ቁጥር በእነ ርሱ ላይ ያለኝን ቅሬታ ለመግለጽ አላትመው ነበር። ይሁንና ደብዳቤሽ ላይ በገለጽሽልኝ የድል ሕይወት ምስጢር መኖር ስጀምር አንዴም በሩን አላላተምኩም፤ የቅሬታም አመለካከት አልነበረኝም።» ብላ መልስ ጽፋለች።

በጋጢአት ላይ ድል ያለ ጥርጥር በጌታ ይከናወንልሃል፤ ስለሆነም ምንም ዓይነት ጥረት ማድረግ አያስፈልግም። እደግመዋለሁ ! ድል በነፃ የሚገኝ እንጂ በጥረት የሚመጣ አይደለም።

የድል ሕይወት ማግኘት እንደ ተዓምራት ይቆጠራል

«የራሳችሁን መዳን ፈጽሙ ስለ በጐ ፈቃዱ መፈለግንም ማድረግ ንም በእናንተ የሚሠራ እግዚአብሔር ነውና» ፊልጵ 2:12–13

ጳውሎስ የራሳችንን መዳን እንደ እግዚአብሔር በጉ ፈቃድ የምንፈጽምበት ምክንያት በቀላሉ እርሱ እንድንፈጽም ስለሚያስችልን ነው ብሎ ይነግረናል። በውስጣችን ተንቀሣቅሶ ቅዱስ መሆን የሚያስችለን እግዚአብሔር ነው። እርሱ ሁሉን በእኛ ውስጥ ፈጽሞ ስለሠራ ቅዱሳን እንሆ ናለን እንጂ እኛ ብርቱ ጥረት ስላሣየን አይደለም። ምክንያቱም ይህ የቅድስና ሕይወት ፈጽሞ ጌታ ራሱ ያከናወነው ሥራ እንጂ የጥረታችን ውጤት አይደለም።

በምድር ላይ ብዙ ሰዎች ያለ ተዓምራት ብልሹነታቸውን ሊያስወግዱ አይችሉም ብዬ ያለማመንታት እናገራለሁ። አንዳንድ ሰዎች ውድቀታቸውን አያውቁም፤ ድካማቸውን አያዩም። ሌሎች ደግሞ በትዕቢተኛ ባሕሪያቸው ላይ ልጓም ሊያደርጉ እንደማይችሉ ይገነዘባሉ። ተአምራት ከሌለ ግናቸውም ወደ ድል አይመጡም። ግነው ኃጢአትን ሊያሸንፍ የሚችል? የሰው መንገድ ኃጢአትን መጨቆን ነው። እግዚአብሔር ሥራውን ሲሠራ ግን በሚያስደንቅ ሁኔታ አሮጌው ሰውነታችንንና ኃጢአታችንን አስወግዶ ንጹሕ ልብን ይሰጠናል። የእግዚአብሔርን ልብ ብንረዳ ምንኛ ደስተኞች በሆንን ነበር!

ከብዙ ሰዎች ይልቅ ስሜቷ እጅግ ኃይለኛ የነበረ አንዲት እህት ነበረች። ባለቤቷና ልጆቿ እንዲሁም የሚያውቋት ሁሉ ይፈሯት ነበር፤ ነገር ግን ክርስቲያን ነበረች። ይህን ስሜቷን ታዲያ ምን ታድርገው? ከብዙ ዓመታት በኋላ ጌታን እንደ አዳኛዋ እንደተቀበለች ሁሉ እንደ ድሏም አድርጋ ተቀበለችው። ልክ ይህንን እንዳደረገች በግሥቱ ፀጉሯን ልታበጥር ወደታችኛው ፎቅ ከመውረዷ በፊት ከባድ ፈተና ገጠማት። ባለቤቷና ሰራተኛው ታችኛው ፎቅ በጣም ውድ የሆነ አምፑል ሊሰቅሉ ሲሞክሩ በንዝህላልነት ሳይሆን አይቀርም አምፑሉን ጣሉትና ደቀቀ፤ ልክ ያን ጊዜ እነርሱ ወዳሉበት ክፍል ወረደች። ባለቤቷ እንዳያትም በቁጣ ትናደዳለች በሚል ፍርሃት በድንጋጤ ተሳቀቀ። ነገር ግን ግንም ከሚጠብቀው ውጭ ረጋ ብላ የደቀቀው አምፑል ተጠርጐ ይነሣ ስትል ሠራተኛውን አዘዘች። ባለቤቷ በጣም ተደነቀ። ወትሮ ትንሽ ስኒ ወይም ሣህን ቢሰበር ትጣላ ነበር። እንዲህ ዓይነቱን ለውጥ ሲያይ ያን ሌሊት በደንብ ተኝታ መሆን አለመሆኗን ወይም ታማ እንደሆን

ጠየቃት። መልሷ እንዳልታመመችና ጌታ አርጌ ማንነቷን እንዳሰመ ገደ ላት ነበር። ባለቤቷ «ይህ ተዓምር ነው! ይህ ተዓምር ነው» በማለት ጮኸ። በእርግጥም ተዓምር ነበረ። እግዚአብሔር ይመስገን!

ሚስተር ቻርለስ ጂ ትርምቡል በዘመኑ የሰንደይ ስኩል ታይምስ ዋና አዘጋጅ ሲሆን በጣም መንፈሳዊ ነበር። ይህ ወንድም የድል ሕይወት ተዓምራት መሆኑን በሚገባ ተቀብሎታል። በአንድ ወቅት ለአንድ የቤተክርስቲያን ሽማግሌ ጌታ ኢየሱስን ወደ ሕይወቱ ስለተቀበለው አንድም ጊዜ ተናድዶ አንደግያውቅና የሚናደድ ዝንባሌም ጨርሶ እንደሌለው መሰከረለት። የቤተክርስቲያን ሽማግሌውም «የቀድሞው ኃጢአተኛ» ሁሉ አሁን የሉም ለማለት ፈልገህ ነውን? አለው። ሚስተር ትሩምቡልም «አዎን እንደዚያው ነው» በማለት መለሰ። ሽማግሌውም «ደህና ይህ በእንተ ሕይወት እውነት እንደሆነ አምናለሁ። ለእኔ ግን እውን ሊሆን አይችልም» አለ። ሚስተር ትሩምብል ሽማግሌው አብሮት ይጸልይ ዘንድ ጠየቀው። በዚያን ተገም ብዙ ጸለዩ በመጨረሻም ሽማግሌው አሁን ደይሆንም ያለው እንደሚሆን ተቀበለ። በሌላም ቀን ሽማግሌው ሚስተር ትሩምቡልን አግኝውና እንዲህ ሲል መሰከረለት! «ያን ምሽት ከአንተ ጋር ጸልዩ እንዳገኘሁት ያለ ነገር በሕይወቴ ጨርሶ አግኝቼ አላውቅም። በእርግጥ ተዓምር ነው። ድልን ለማግኘት መታገልና ኃይልን ማፍሰስ አያስፈልግም። በእውነት ይህ አስደናቂ ተዓምር ነው» አለው። ከዚያም በኋላ ትንሽ ቆየት ብሎ በሚሠራበት ቦታ በቦርዱ አባላት መካከል ከፉ ተፅዕኖ እንዳለበት ነገር ግን መታገሥ እንደምለ ለሚስተር ትሩምቡል ጻፈለት። እንዴት ያለ ተዓምር ነው!

ወገኔ ሆይ! መፍታት ያቃተህ ችግር ወይም ልትተወው ያስቸገረህ ኃጢአት ካለ ጌታ ኢየሱስ በእንተ ሕይወት ተዓምር ይሠራል። ለዓመታት ተስፋ ያስቆረጠህን ጉዳይ በእንዲ ይፈታዋል። ምንም ዓይነት ኃጢአት ይሁን የመንፈስ ወይም የሥጋ ወይም የሐሳብ ወይም የአካል ወይም የባሕርይ ወይም የእግዚአብሔርን ፈቃድ አለማድረግ ወይም አለመለየት ወይም ለመናዘዝ መቸገር ይሁን ጌታ የኃጢአቱን ምንነት ሳይመለከት ተዓምር ይሠራልሃል። ራስህን ለእግዚአብሔር ልትቀድስ አትችልም፤ እርሱ ግን እንድትቀደስ ያደርግሃል። በራስህ መታገሥ

አትችልም! እርሱ ግን ታጋሽ ያደርግሃል። እግዚአብሔር በተዓምራቱ ማንኛውንም ኃጢአት ድል መንሣት ይችላል።

የድል ሕይወት የተሸፈነ አይደለም

የድል ሕይወት ውጤት የሚታየው ተገልጦ እንጂ ተሸፍኖ አይደለም። በራሳችን የሚገኝ ድል ሁልጊዜ ራሳችንን በመጨቆን የሚገኝ ነው። ትክክለኛው የድል ሕይወት ግን በነፃ ስጦታ የሚገኝ ነው። እኔ በምናርበት አካባቢ አንዲት በዕድሜ ጠና ያለች ሴት ነበረች። ይህችም ሴት የሚያሳዝናት ነገር ሲያጋጥማት የውስጥ ስሜቷን ጨቁና ላይ ላዩን ፈገግ ያለ ፊት ታሳይ ነበር። እንዲህ ያለውን የተጨቆነ ሕይወት ለተወሰነ ጊዜ ከኖረችበት በኋላ በውስጧ ታምቆ ደም መትፋት ጀመረች። ይህች ሴት በስተመጨረሻ ለምን ደም መትፋት ጀመረች? ችግሩ በውስጧ ታምቆ ስለቀረ ነው። በክርስቲያን ሕይወት ያለው እውነተኛ ድል ግን የተገለጠ እንጂ የታመቀ አይደለም። የተገለጠ ሕይወት ጌርሶ የተገኘውን ነገር የመግለጥን ነገር ያመለክታል። ይህ በፊሊጲስዩስ 2፡12 «ደኅንነታችሁን ፈጽሙ» በማለት የተነገረውን ያሣያል። ቀደም ሲል ራሳችንን ለመሸፈን በኃይል ጥረናል፤ አሁን ግን በእኛ ውስጥ የሚደረገውን የክርስቶስን ድል እንገልፃለን። ክርስቶስ በእኔ ስለሚኖር በዓለም ፊት እርሱን እገልጣለሁ።

ሚስስ ፔን ሌዊስ ግጥም የመግጠም ችሎታ ያላትና ሕፃናትን ወደዚህ የድል ሕይወት በመምራት የተካነች አንዲት ወጣት ጓደኛ ነበራቻት። አንድ ቀን ሚስስ ፔን ሌዊስ ሕፃናቱን እንዴት እንደምትይዛቸው ለማየት ወደዚች ወጣት ሄደች። በዚያን ቀን ይህች ወጣት ከአሥር የሚበልጡ ሕፃናትን ምግብ ጋብዛ ነበር። ልክ በልተው ጠረጴዛ ከመፅዳቱ በፊት ፔን ሉዊስ በሥፍራው ደረሰች። ወጣቷም ሕፃናቱን «ይህን ቆሻሻ ምን ማድረግ ይቻላል?» አለቻቸው። እነርሱም ለመምህራቸው በንጹሕ የጠረጴዛ ልብስ እንዲሸፈን ሐሳብ አቀረቡ። እርሷም እንደተባለችው አደረገች። እንግዳ ሆና ሕፃናቱን እንዴት እንደምትይዛቸው ለመገንዘብ የመጣችው ፔን ሉዊስ ከሄደች በኋላ ወጣቷ ልጆቹን እንግዳዋ በጠረጴዛው ላይ ያለውን ፍርፋሪና የተንጠባጠበውን ወተ ማየት አለማየቷን

ጠየቀቻቸው። እነርሱም አላየችውም በማለት መለሱ። በመቀጠልም ልጄ ቸን እንዲህ በማለት በጥያቄ ያዘነቻቸው፤ «ምንም እንኳ እንግዳዋ ፍርፋሪውንና የተንጠባጠበውን ወተ ያላየች ቢሆንም ጠረጴዛው ንጹሕ ነው ትላላችሁ?» መልሳቸው ግን «እንግዳዋ ምንም ነገር ያላየች ቢሆንም ጠረጴዛው ግን ቆሻሻ ነበር» የሚል ነበር።

እዚህ ላይ ብዙ ሰዎች ውጫቸውን እንጂ ውስጣቸውን ንጹሕ ለማድረግ የተነሱ እንዳልሆኑ መናገር እፈልጋለሁ። ማለው የልብ ሐሳብ ስሜቱን መግለጥ የሚደፍር፣ ይህም ሆኖ ራሳችንን እንደ ድል ነሽ እንቆጥራለን። ሰዎች እንዲያመሰግኑን ጨኖና አንገት ደረ ለመሆን እንሞክራለን። ታጋሽ ለመሰል ታጋሽ አለመሆናችንን በሽሩን እንደብቃለን። እዚህ ላይ በግልጽ እናገራለሁ። በውስጥ የተጨቆነ ነገር ሁሉ ድል አይደለም፤ ከእኔነታችን ስንወጣና በምትካችን ክርስቶስ ሲገባ ያኔ ድል ይኖረናል። በዚህ ጊዜ የሚገለጥ ሁሉ ድል ነው።

ለምሳሌ አንድ ፍራፍሬ እያዞረ የሚሸጥ ሰው ወደ አንተ መጥቶ ፍራፍሬ እንድትገዛው ይጠይቅሃል እንበል። ነገር ግን ምንም ላትገዛው ትመልሰዋለህ። እንደገና ሁለት ሦስት ጊዜ መጥቶ ሲጠይቅህ ፍራፍሬውን አይተህ አልገዛም፣ አመሰግናለሁ ብለህ በመለስከው ቁጥር ብስጭቱን በውስጡ ጭምቅ ያደርጋል። ይህ ድል አይደለም፤ የንግድ ዘዴ እንጂ። የክርስቶስ ድል ግን ልብን እንኳን ያነፃል። በእጥፍ ድል ንጹሕ ልብ ነው።

በቼር ውስጥ የሚኖር ዕድሜው ከሃምሳ ዓመት በላይ የሆነ አንድ ወንድም አውቃለሁ። ይህ ወንድም የኮንፊሽስን እምነት ሥነ ጽሑፎች ወይም የቻይና የፍልስፍና አስተማሪዎችን ሥነ ጽሑፍ በዕድሜው ሙሉ አጥንቷል። በጌታ ካመነ ሦስት ዓመት ቢሆነውም የደሰሰውን ደምና ከኃጢአት የማንፃት ኃይሉን ብቻ ነው የሚያምነው። ጌታን ከተቀበለ በኋላ ባለው ሦስት ዓመት ውስጥ በኮንፊዩሽያኒዝምና በክርስትና መካከል ያለውን ዋና ልዩነት ፍጽሞ አላወቀውም። የኮንፊሽስ ተከታይ ስለሆነ በትዕግሥት ለመሥራትና ራሱን በመቆጣጠር ለመሻሻል ይሞክራል። በዚህም ጥረቱ ውጤት ካመጣ «የልምምድ ጠቢብ» የሚል ስያሜ ያገኛል። ይህ ወንድም ክርስቲያን ከሆነ በኋላ እነዚህን ልምምዶች ያደርግ

ክር።ትልቁን ችግር እንደ ትንሽ መቁጠር፣ አነስተኛውንም ነገር እንደ ምንም በመቁጠር የክንፈሽሰን አመለካከት ይዞ ቀጠለ። በጓላ ላይ የክር ስቲያን ድል የሚገኘው ራስን በመጨቆን ሳይሆን ክርስቶስን ድላችን አድርጉ በመቀበል እንደሆነ ሲገባው የድልን በር አቋረጠ። ከዚህ በፊት የክርስቶስ ድልም በሕይወቱ እንዳልነበረ መሰከረ። ክርስትና ከሌሎች ሃይማኖቶች ጋር ሲተያይ ምንኛ ሰፊ ልዩነት አለው። በመስቀል ላይ በክርስቶስ ሞት የተመሰከረው ክርስትና ከሌሎች ሃይማኖቶች ልዩ እንደ ሆነ ብቻ ሳይሆን ክርስቶስም በእኛ ስለሚኖር ክርስትና ከሌሎች ሃይማኖቶች ልዩና ውብ ነው። ስለዚህም የደኅንነትን መንገልና በተለይም በድል እንድንኖር በእኛ ምትክ የሚኖረውን ክርስቶስን እንሰብካለን። ቀደም ሲል ይህ ወንድም በራሱ ላይ ጥብቅ ቁጥጥር በማድረግ ታማኝ የሆነ የክንፈሽሰስ ደቀ መዝሙር ነበር። አውነ ግን ራሱን ከራሱ አስወጥቶ ክርስቶስ በእርሱ ምትክ እንዲኖር ፈቅዷል? ያለ መጨቆንና ያለ ሽንፈት።

ከላይ ያሉት አምስት ነጥቦች ድል የሚነሣውን የዚህን ሕይወት ባሕርይ ይገልፃሉ። በመደምደሚያ ሙልክ ግን ትንሽ ታል ጨምራለሁ። ይህንን አስታውስ! ልክ እንደ ደኅንነት ድልም የምዝገባ ቅፅ አለው። በአንድ በሆነ ዓመት፣ በአንድ በተወሰነ ወር በአንድ በሆነ ቀን ድነሃል። ይህን ስል አንዳንድ ሰዎች ቀኑን ሊረሱ ወይም እርግጠኛ ላይሆኑ እንደሚችሉ ግን እገነዘባለሁ። ልክ እንደዳንከበት ዓመት፣ ወርና ቀን ወደ ድል የገባህበትም ዓመት፣ ወርና ቀንን መመዝገብ አለብህ። ምክንያቱም ድል ወደ አሸናፊነት ሕይወት የምትገባበት በር ስለሆነ ነው። ግንም ሰው ለመዳን ምንም ያህል አልቀረውም አይባልም። ዳነ ከተባለ ዳነ ነው። እንዲሁም ግንም ድል ሊነሣ ትንሽ ነው የቀረው አይባልም። ድል ድል ነው። ለማሸነፍ ምንም አልቀረውም ግለት እንደ አውነቱ ከሆነ ማሸነፍ አለመቻል ነው። ስለዚህም ሁላችንም ይህን የድል በር ግለፍ አለብን።